

መስቀል ኃይላችን ነው!

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ፤ በሕዝብ ግንኙነት መምሪያ የተዘጋጀ

ማውጫ

02 የመጽሔቱ መልእክት
04 የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አባታዊ መልእክት
07 የብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ መልእክት
10 የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መልእክት
11 የመንፈሳዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት
13 የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት
16 “ዘኢጸረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ዩጸመደኒ ÷ መስቀሌን ሊሸከም የማይወድ ሊከተለኝ አይችልም።” (ሉቃ.14÷27)
20 “እንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜኅር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ አግዚአነ ÷ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ።” (ገላ. 6÷14)
24 “የጽኑ ተስፋችን መሠረት መስቀል ነው።” (2ኛ ጴጥ. 1÷4፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)
30 “ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበምድር ወለዘበሰማያት ÷ በምድርም በሰማያት ላሉ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ።” (ቈላስ. 1÷20)
34 “ኢትዮጵያንና ሳባን ለእንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ።” (ኢሳ. 43÷3)

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ሥዩማን አስክንድር ገ/ክርስቶስ

ኮምፒዮተር ጽሑፍና ዝግጅት
ሳዕከ ሰላም ነቢየ ኤልያስ

ግራፊክስ ዲዛይን
ተመስገን ቶማስ


ትርጉም
መምህር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር)
ወ/ሪት ዮርዳኖስ አዳሴ

ፎቶግራፍ
መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ

ጎትመት
ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

© መስከረም ፲፯ ቀን ፭፻፲፱ ዓ.ም
አዲስ አበባ÷ ኢትዮጵያ

የመጽሔቱ መልእክት



መስቀል ኀይላችን ነው!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መስቀል የመዳን፥ የድልና የነፃነት ምልክት መሆኑን በማመንና በማስተማር በዓለ መስቀልን በየዓመቱ ትዘክራለች፤ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐትም በአደባባይ ታከብረዋለች። «መስቀል ኀይላችን ነው» ስትልም ጽንሰ ሐሳቡ ጥልቅ መንፈሳዊ፥ ሕይወታዊና ሰብኣዊ ትርጉሞችን አጣምሮ የያዘ እውነት መሆኑን በማጽናት ነው።

መስቀል በጥንት ዘመን እጅግ አሰቃቂ የቅጣት መሣሪያ በመሆን ያገለግል የነበረ ሲሆን፤ የወንጀለኞችና የዐመፀኞች መጨረሻ ተደርጎም ይታሰብ ነበር። ነገር ግን ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበደላችን ምክንያት የተጣለብንን የሞት ፍርድ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ በከፈለልን የሕይወት ዋጋ፥ ያ የወንጀለኞች መቅጫና የዐመፀኞች መጨረሻ በመሆን ያገለግል የነበረው መስቀል የሰላም፥ የፍቅር፥ የይቅርታና የድል ምልክት ሆነ።

ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ በደልና ኀጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፥ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፥ ክቡር ደሙን አፍስሶ የዕዳ ደብዳቤያችንን ደምስሷል።መስቀል ጌታችን ስለ ፍጥረት ሁሉ ያለውን ጥልቅና ወሰን የሌለው ፍቅር ያሳየበት መንበር ነው። በመስቀሉ ደም አማካኝነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሷል። ቅዱስ

መስቀል ኀይላችን ነው!

ጳውሎስ፦ «ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፥ እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ» (ገላ. 6፥14) በማለት፥ መስቀል የክርስቲያኖች ትምክሕትና የሕይወት መሠረት መሆኑን አረጋግጦልናል። መስቀል ለክርስቲያኖች የድል አክሊል፥ የሕይወት መሠረትና የሰላም መንገድ መሆኑ የተረጋገጠውም ጌታችን ስለእኛ ድኅነት በመስቀል ላይ በከፈለው መሥዋዕትነት ነው።

የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዐት መሠረት ታላቅ መንፈሳዊና ባህላዊ ሀብታችን በመሆኑ በዓሉን ስናከብር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ቅዱሳን ሐዋርያትና ሰማዕታት በመስቀሉ ፍቅር ያሳዩንን እምነትና ተጋድሎ እያሰብን መሆን ይገባል።

የአይሁድ ሕዝብ በቅናት ተነሣሥተው ክቡር መስቀሉን አርቀው በመቆፈር ከቀበሩት በኋላ፥ በላዩ የቆሻሻ ክምር እንዲጫን በማድረግ ደብዛው እንዲጠፋ አድርገው የነበረ ቢሆንም፤ ንግሥት ዕሌኒ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና በአረጋዊው ኪራኮስ አማካኝነት ደመራ ደምራ ዕጣን በላዩ በመጨመር ጢሱ ወደላይ ወጥቶ ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በመጥቀሱ፥ ለዘመናት ተቀብሮ ከነበረበት የቆሻሻ ክምር ሥር ቆፍራ ያስወጣችበትን ታሪካዊ ክሥተት ለመዘከር፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የደመራ በዓልን በከፍተኛ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት በአደባባይ በድምቀት ታከብራለች። መስከረም 17 ቀን ደግሞ የመስቀል በዓል ይከበራል።

የመስቀል ደመራ መንፈሳዊ የአደባባይ ክብረ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበና ኢትዮጵያን ለዓለም እያስተዋወቀ ያለ ታላቅ ሀብታችንና ኩራታችን ሲሆን፤ ለሀገራችን ኢትዮጵያም የቱሪዝም መስሕብ በመሆን በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚታደሙበት ከመሆኑ ባሻገር ለሀገራችን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እየሆነ ይገኛል።

ውድ ኦርቶዶክሳውያን ወገኖች!

በዓለ መስቀልን ስናከብር በደመራው ዙሪያ ተሰባስበን መብራት በማብራትና መዝሙር በመዘመር ብቻ መሆን የለበትም። የመስቀሉን እውነተኛ መንፈስና ትርጉም በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ከመግለጽ ባለፈ በዓሉ ትውፊቱን እንደጠበቀ ለትውልድ እንዲተላለፍ ዘመኑ ያፈራቸውን መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የበዓሉን ታላቅነት በተለያዩ ቋንቋዎች አጉልተን በማስተዋወቅ ጭምር መሆን እንደሚገባው ልብ ልንል ይገባል።

ነገረ መስቀሉን ስናስብ ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ «አባት ሆይ፥ የሚደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት ያስተማረንን የይቅርታና የሕይወት መንገድ ልንከተል ይገባል። ሀገራችንና ሕዝባችን በሰላም፥ በምሕረትና በፍቅር ይኖሩ ዘንድ ክርስቲያኖች የሰላም መሣሪያዎች መሆን አለብን። መስቀል ቀጥተኛውና አግድም እንጨቶች ተገናኝተው አንድ እንደሚሆኑ ሁሉ፥ ሰማያዊውን ከምድራዊው፥ ሰውን ከሰው ጋር የሚያገናኝ የአንድነት ማሰሪያ ነው። ልዩነቶችን አስወግደን በክርስቶስ ፍቅር አንደኛችን ሌላኛችንን ልንደግፍ ይገባል። የተራቡትን በማብላት፥ የተጠሙትን በማጠጣት፥ የታረዙትን በማልበስና ያዘኑትን በማጽናናት የክርስቶስን ፍቅር በግብር ማሳየት አለብን።

በዓለ መስቀሉን ስናከብር አደባባይ ወጥተን ደመራ በመደመር፥ ችቦ በማብራትና በደስታ በመዘመር ብቻ መሆን የለበትም። ይልቁንም የመስቀሉን እውነተኛ ትርጉም በልባችን በመጻፍ ሊሆን ይገባል። በመስቀል ደመራ በዓል ላይ ስንሰባሰብ ሁላችንም ጌታችን ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ያሳየንን ፍቅር በማሰብ፥ ትእዛዙን በመጠበቅ፥ ሃይማኖታችንን በማጽናትና ለሀገራችን ሰላምና አንድነት በጽኑ በመጸለይ መሆን ይኖርበታል።

መስቀል ኀይላችን የሚሆነው፦ ይቅርታ ማድረግ ሲያቅተን የመስቀሉን የይቅርታ ኀይል ስንማጸን፤ ፈተናዎች ሲበዙብን በጽናት ለመቆም የመስቀሉን ታላቅነት ስናስብ፤ የተራቡትንና የተቸገሩትን በመርዳት የመስቀሉን የፍቅር መንገድ ስንከተል ነው።

እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላምና በጤና አደረሳችሁ! የመስቀሉ ሰላም፥ ፍቅርና ኀይል ከሁላችን ጋር ይሁን።

ለቀ ስዩማን እስክንድር ገብረ ክርስቶስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ዋና ኃላፊና
የቤ/ሕ/አ/ል/ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ

መስቀል ኀይላችን ነው!



መስቀል ኀይላችን ነው!

የክቡር ወቅዱስ ፓትርያርኩ ኅተመ መልዕክት



“ወነገረ መስቀሉሰ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ፤ የመስቀሉ ነገር የእግዚአብሔር ኃይል ነው”

1ቆሮ. 1÷18

መስቀል የሚለው ቃል ቀጥተኛ ፍቺ መሰቀል፥ መንጠልጠል፥ በሁኔታውም ሥቃይ የበዛበትን መከራ መቀበል ማለት ነው። ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቀለ ሲባል ይህ ዓይነቱን መከራ ተቀበለ ማለት ነው። የጌታችን ነገረ ተሰቅሎ መከራን ከመቀበል ባለፈ ብዙ የነገረ መለኮት ምሥጢራትን ያዘለ ነው። የጌታችን ነገረ ተሰቅሎ በመከራ ተነሥቶ በኀይለ ሕይወት የተጠናቀቀ ነው። በሌላ አባባል የመስቀሉ ነገር መነሻው መከራ ፍጻሜው ግን ድኅነት ነው ማለት ነው። የመስቀል የመጨረሻ ውጤት ፍጹም ድኅነት ሆኖ በመገኘቱ ከመከራው ይልቅ ድኅነቱ ጎልቶ መነገሩ ትክክል ይሆናል፤ ‹‹ትክክለኛ ሳቅ የመጀመሪያዋ ሳትሆን የመጨረሻዋ ናት›› የሚለው አባባል ከመስቀሉ ውጤት ጋር ይስማማል።

እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አጠቃላይ አስተምህሮ ነገረ መስቀል ማለት ‹‹ነገረ ሕማም ወድኅነት›› ማለት ነው። የጌታችን የመከራ መስቀል ጉዞ በሕፃንነቱ ዘመን በስደት አንድ ተብሎ ተጀምሮ በመስቀል ላይ በሞት የተጠናቀቀ ነው (ማቴ. 2÷13)። በመሆኑም በዚህ ረጅም ዘመን የነበረው ውጣ ውረድ በሙሉ የነገረ መስቀሉ ወይም የመከራ መስቀሉ አካል ነው።

ጌታችን በዘመነ ስብከቱ ያስተማረው የትምህርተ ወንጌል ነገረ ድኅነትም በመስቀል የሚታተም መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ የመስቀሉ አካል ነው፤ የመስቀሉ ቃል ተብሎም ይገለጻል። ጌታችን ሰው የሆነበትን ምክንያት በቅዱስ ወንጌል አስረግጦ ሲያስተምር፦ ‹‹የሰው ልጅ ሊያገለግል፥ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም ብሎ ነግሮናል።›› (ማቴ. 20፥28)

መስቀል ኀይላችን ነው!

በትክክልም የጌታችን ሰው መሆን፥ ማገልገልና ቤዛ መሆን በሚሉት በሁለቱ ዓበይት መልእክቶች ይጠቃለላል፤ ይኸውም ማስተማሩን፥ በሽተኞችን መፈወሱን፥ ለኀጢአተኞች ስርየት መስጠቱን፥ ኀብስትን ኣበርክቶ መመገቡን፥ ሙታንን ማንሣቱን ወዘተ... አገልግሎቱን ያመለክታሉ። በሥጋው የተቀበለውንና በመስቀል ላይ ያጠናቀቀውን መሥዋዕትነት ደግሞ ቤዛዊነቱን ያመለክታል፤ እነዚህ ሁሉ የመስቀል ኣካል ናቸው።

ጌታችን ከኀጢአት፥ ከሞት፥ ከመቃብርና ከዲያብሎስ ጋር ያካሄደው የፍልሚያ ስልት መንፈሳዊ፥ ሕጋዊና ሞራላዊ ልዕልናን መርሕ ያደረገ ነው። ይህ የፍልሚያ ጠባይና ስልት እኛ ሰዎች ከምናውቀውና ከለመድነው ፍልሚያ ፍጹም የተለየ ነው። እኛ የምናውቀው ፍልሚያ በቁሳዊ መሳሪያዎች ጠላትን ደብድቦ መግደል ነው፤ የጌታችን ፍልሚያ ግን እንከን በማይገኝለት ሁለንተናዊ ኣገልግሎት የሰውን አእምሮ በመማረክ በማሳመንና ሕግ የሚጠይቀውን በማሟላት ለጠላት ሕጋዊ መደላድልን ማሳጣት ነው።

እኛ ሰዎች ለሸንፈት የተዳረግነው ሕግን በማፍረሳችን ነው፤ ሕግ ማፍረሳችን መግቢያ ሆኖአቸው ኀጢኣት፥ ሞት፥ መቃብርና ዲያብሎስ ተጠራርተው ያለ ምሕረት በአንድነት ቀጠቀጡን (ሮሜ 5÷12)። እነዚህን መፋለም የሚቻለው በቁሳዊ መሳሪያ ሳይሆን የሕግን ክፍተት በመዝጋት ብቻ ነው፤ ሕግ ኀጢኣተኛን አስመልክቶ የሚጠይቀው ቅጣት ሞት ነው (ሮሜ 6÷23)። ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹ኀጢኣትን የምትሠራ ነፍስ እሷ ትሞታለች›› ብሎ በዓዋጅ ነግሮናልና ነው (ሕዝ. 18÷4)።

ስለሆነም ሕጉ የጠየቀው የሞት ቅጣት ሲፈጸም ነፃነቱ እንደሚገኝ ታውቆ ያደረ ነበር፤ ይህም በመሆኑ ኦሪታዊው ሕግ ኀጢኣትን በቤዛዊ ሞት ይቅር እያስባሉ፥ እስከ ክርስቶስ ድረስም እያስተማረና እያለማመደ ቈየ (ዘሌ. 5÷17-19)፤ በዚህም ‹‹ደም ሳይፈስ ስርየት የሌለ›› መሆኑን አረጋገጠ (ዕብ. 9÷22)።

ሕግ ከሰዎች የሚጠብቀውን ሞት ራሱ ጌታችን በሰዎች ፈንታ በመስቀል ላይ ስለተቀበለ፥ ሕግ ሰዎችን በቅጣት የሚይዝበት ሕጋዊ ሥልጣን ኣጣ፤ በዚህ ምክንያት ኀጢኣት፥ ሞት፥ መቃብርና ዲያብሎስ ተሸንፈው ባዶ እጃቸውን ማለትም ሰውን የሚቀጡበት ሕጋዊ ሥልጣን አጡ (1ቆሮ. 15÷53-57)። በውጤቱም ሰዎች ከኀጢኣት፥ ከሞት፥ ከመቃብርና ከዲያብሎስ ነጻ ሆነው በቀጥታ ወደ ገነት ገቡ (ሉቃ 23÷43)፤ በዚህ ሂደት ሕይወት ተገኘ፤ የመስቀል መነሻው መከራ፥ ፍጻሜው ግን ድኅነት ነው የሚባለው ከዚህ ኣኳያ ነው፤

ከዚህ አንጻር የመስቀሉ የመጨረሻ ውጤት ይቅርታን፥ ምሕረትን፥ ሰላምን፥ ኣንድነትን፥ ነፃነትን ገንዘብ ማድረግ፥ በኀጢአት፤ በሞት፥ በመቃብርና በዲያብሎስ ላይ ድል መቀዳጀት ሆኖ ተገኘ፤ እንደዚህ ያለ ኃይል ደግሞ ከእግዚአብሔር እንጂ ከፍጡር ወገን ኣይገኝምና የመስቀሉ ነገር ለማዳን የተደረገ የእግዚአብሔር ኃይል ነው ተብሎ ተመሰጠረ።

የሽፍታውን ኃጢኣት በይቅርታ ሰርዞ ዛሬውኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ ያለ መቃብርን ከፍቶ የሞቱትን ሰዎች ያነሣ(ማቴ. 27÷52) ኣንተ ርኩስ መንፈስ እልሃለሁ ከእርሱ ውጣ ብሎ ዲያብሎስን ያስወጣ(ሉቃ. 4÷35) ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ነው፤ የሰው ኃይል ይህንን ማድረግ ኣይችልምና።

ስለሆነም የጌታ ቀን እስኪደርስ ከምድራዊ ኑሮኣችን ተለይተን ወደ እርሱ የምንሄድበት ጊዜያዊ ሞትና መቃብር ቢኖርም፥ ለዘለቄታው ግን በጌታችን ቀን ሞትም፥ መቃብርም ለኣንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግደው ፍጻሜ በሌለው ኃይለ ሕይወት ከጌታችን ጋር በመንግሥቱ የምንኖርበት ዕድል ተዘጋጅቶልናልና ጠላቶቻችን በእውነት ተሸንፈዋል።

በዛሬው ዕለት በከፍተኛ የግብረ ማኅበር ሥርዓተ ኣምልኮ እግዚአብሔርን በማመስገንና በማምለክ የምናከብረው በዓለ መስቀል፥ ይህንን ነገረ ድኅነት ለሰው ልጆች ለማብሰርና ለማወጅ ነው፤ የመስቀሉንም ነገረ ድኅነት በክብር ጠብቀን ለመጪው ትውልድ ለማውረስና ለማስተላለፍ ነው፤ ለዚህም መነሻ ምክንያታችን በዓመፅ ተቀብሮ የነበረውን እውነተኛውና ዋናው መስቀል የተገኘበትን ተኣምራዊ ክሥተት ነው።

ዕፀ መስቀሉ የነገረ ድኅነቱ ቀዋሚ ምስክርና ኣንደበተ ርቱዕ ሰባኪ ነውና በቤተ ክርስቲያን ለዘላለሙ እየተከበረ ይኖራል፤ ዕፀ መስቀል በጫንቃው የተሸከመውን ነገረ ድኅነትንም እናስብበታለን፤ እናስታውስበታለንም፤ በጌታችን ተሰቅሎ መዳናችንንም በረቀቀ ዓይነ መንፈስ እናይበታለን።

እግዚአብሔር የተባረከና የተቀደሰ በዓል ያድርግልን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ፤

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፤

አባ ማትያስ ቀደማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

መስከረም ፲፯ ቀን ፭፻፲፱ ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤



የብፁዕ ጠቅላዩ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት

አስመ ውእቱ ሰላምነ፡ ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልኤሆሙ፣ ሕዝብና አሕዛብን አንድ ያደረገ ሰላማችን እርሱ ነው።

(ኤፌ. 2፡14)

በየዓመቱ መስከረም ዐሥራ ስድስትና ዐሥራ ሰባት ቀን የምናከብረው የደመራና የመስቀል በዓል የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀበትን፥ የፍቅርና የሰላም ውል በደሙ የታተመበትን ታላቅ አምላካዊ ውለታ የተሠራበትን መስቀል የምናስብበት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መስቀልና ዕርቅ በተናገረበት ድርሳኑ እንደሚያስተምረን፦ «መስቀል ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበት ሰላማችን ነው፤ መስቀል የሰው ልጅ ድኅነት የተፈጸመበት፥ ውድቀት አልፎ ምሕረት፥ ጥላቻ አልፎ ፍቅር የነገሠበት ታላቅ የሰላም መድረክ ነው»። ቅዱስ ያሬድም በንጢአት ተጎድቶ የነበረው ዓለም የዳነበት መስቀል ለክርስቲያኖች ክብርና ጌጣቸው መሆኑን ሲናገር፦ "ዮም መስቀል አሠነየ ዓለመ እንተ በልየ በሥነ ማርያም አዋከየ ለክርስቲያን ኮኖሙ ዕበየ" ብሏል።

ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ነሥቶ ሰው የሆነው አምላክ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የጥላቻን ግድግዳ አፍርሷል። በርእሱ ያነሣነውና ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ፦

መስቀል ኀይላችን ነው!

«እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን አንድ ያደረገ የጥላቻንም ግድግዳ በመስቀሉ ያፈረሰ» (ኤፌ. 2፥14) በማለት እንደገለጸው፥ መስቀል የሕብረት፥ የሰላምና የዕርቅ ምልክታችን ነው። በመስቀሉ ጥል ተወግዷል፥ ከሰው የማይገኘው እውነተኛ ሰላም ተመሥርቷል፥ የራቀው ቀርቧል፥ ታላቅና ታናሽ በሚል ይፈረጅ የነበረ ወገንና ሕዝብ ዕኩልነቱ ተበሥሯል። ዛሬ ለዓለም ሁሉ የሚያበራው ብርሃን፥ እርሱ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ስለእኛ ባደረገው ነገር ሕይወታችን በብርሃን ተመርቷል። በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የምናከብረው የመስቀል ደመራ የእውነተኛው የብርሃን ክርስቶስንና የመስቀሉን ኃይል በእምነት የምንመሰክርበት ነው።

የተወደዳችሁ የቤተ ክርስቲያናችን ልጆች፡-

ዛሬ መስቀሉን ስናስብና ስናከብር በውስጣችን ያለው ጥላቻ፥ መለያየትና የጥርጣሬ መንፈስ አስወግደን በሰላም መንፈስ ከፍ ብለን መሆን አለበት። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ሰላምን አስመልክቶ ባስተማረው ትምህርት፦ «ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የምንችለው ከወንድማችን ጋር ስንታረቅ ብቻ ነው» ይላል። መስቀል የወደቁትን የሚያነሣ፥ የተጣሉትን የሚያስታርቅ እንጂ ሰውን ከሰው የሚለይ አይደለም። የክርስቶስ መስቀል አራቱ አቅጣጫዎች የዓለምን ሕዝብ ሁሉ በአንድነት የሚሰበስቡ በፍቅር የተዘረጉ እጆች ናቸው። መስቀል ፍቅርን እንጂ በቀልን አያስተምርም። በመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታችን «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃ. 23፥34) በማለት ለበደሉት ይቅርታን እንደሰጠ፥ እኛም ዛሬ የክርስቶስ ተከታዮች ሆነን ይቅር ማለትን፥ መቻቻልንና ወንድምን መውደድን ገንዘብ ልናደርግ ይገባል። በተለይም በዚህ በዓል በየመካከላችን ያሉትን ድሆች፥ ወላጅ አልባ ሕፃናትን፥ በሕመም ላይ ያሉትንና የታሠሩትን በማሰብ በፍቅር ልንጎበኛቸው ይገባል። እውነተኛ የበዓል ደስታ የሚገኘው ያለንን አካፍለን የሌሎችን ዕንባ ስናብስ ብቻ ነው።

በአሁኑ ወቅት ዓለማችንና ሕዝቦቿ ከምንም በላይ ሰላም፥ ፍቅርና አንድነት የሚያስፈልጋቸው ወቅት ላይ እንገኛለን። የሰላም አምላክ ክርስቶስ በወንጌሉ «ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ» (ዮሐ. 14፥27) እንዳለ፥ በቅዱስ መንፈሱ፥ በመስቀሉና በቤተ ክርስቲያኑ የምንኖርበትን ሰላሙን ሰጥቶናል። ነገር ግን ለእኛ ለተቀባዮቹ ሰላም በቃል ብቻ የሚነገር ሳይሆን በግብር የሚገለጥ እውነት ነው። ስለዚህ የክርስቶስ ሰላም በየዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ሊገለጥ ይገባል፡ ፡ በልዩነቶቻችን ላይ አተኩረን መቃወምና መጠላላት ያፈርሰናል፤ ሕዝብንም ይበትናል። ስለዚህ ወገኖቻችን ሁሉ ከጥላቻና ከመጎዳዳት ይልቅ ዕርቅን እንዲያስቀድሙ አባታዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ተስፋዎች የሆናችሁ ወጣቶችም በስሜትና በሥጋዊ ሐሳብ ሳትሸነፉ በመስቀሉ ፍቅር ታንጻችሁ ለአንድነት፥ ለሰላምና ለልማት እንድትቆሙ አደራ እንላለን።

አባቶቻችን በሰላምና በፍቅር ያቆዩልንን ትውፊት፥ ታሪክ፥ ባህልና ይህን የመሰለውን የመስቀል አከባበር መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ታሪካዊና መንፈሳዊ ኀላፊነት አለብን። ይህ በዓል ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን በክፋት ከተቀበረበት ካስወጣችበት ጊዜ ጀምሮ፥ በተለይ ግማደ መስቀሉ ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን ወዲህ በተለየ ደማቅ ሁኔታ በመላ ሀገራችን ሲከበር ቆይቷል፡ ፡ ቤተ ክርቲያናችን በዓሉ የሚከበርበትን ሥርዓትና ሀገራዊ ዕሴቱን ጭምር ጠብቃ ለዛሬው ትውልድ ተጠቃሚነት አድርሳዋለች። እኛ ደግሞ ይህን ታሪክ መጠበቅና ማስጠበቅ፥ ለቀጣዩ ትውልድም ማስተላለፍ ይጠበቅብናል። በመስቀሉ የቀደመው ሕይወታችንን አስከፊነትና በክርስቶስ ያገኘነውን ድኅነት እያሰብን ልናመሰግን ይገባናል። የመስቀሉ በዓል የሰላም አየር የሚነፍስበት፥ የፍቅር ዘር የሚዘራበት ሊሆን ይገባል። ይህን የመስቀል በዓል ልብ በመንፈሳዊነት የሚለወጥበት በዓል እናድርገው፥ የጥላቻን ጨለማ በፍቅር ብርሃን፥ የመለያየትን ግንብ በዕርቅና ሰላም እናፍርሰው።

አምላክ ቅዱሳን እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን በሰላም፥ በፍቅርና በአንድነት ይጠብቅልን፤ ሕዝባችንን ከአባር፥ ከቸነፈር፥ ከጦርነትና ከእርስ በርስ መለያየት ይሰውርልን፤ የበዓሉን በረከትና ረድኤት ለሁላችንም ያብዛልን።

በዓለ መስቀሉን የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት ያድርግልን!

አባ ሳዊሮስ

የመንበረ ፓትያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ

የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር ከተማ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ መልእክት

«ወቦቱ ይሣሀሉ ለኩሉ ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ÷ ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀሉ ባፈሰሰው ደም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምን አደረገ።»
(ቈላስ. ፩÷፩)

የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በክርስትና ሕይወት ውስጥ የድኅነት ምሥጢር÷ የሰላም÷ የፍቅር÷ የድል ምልክትና የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረት ነው። በመስቀሉ የተገለጠው የእግዚአብሔር ወሰን የለሽ ፍቅርና ሰላም ለሰው ልጅ የተከፈለ የደም ዋጋ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀል ሲያብራራ÷ ‹‹እስመ ነገረ መስቀሉስ አበድ ውእቱ በኀበ ኀጕላን ወበኀቤነስ ለእለ ድኅነ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ --- የመስቀሉ ቃል ለሚጠፋ ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው” በማለት የመስቀሉን ምሥጢራዊ ጥልቀት በሰፊው አስተምሮናል። (፩ቆሮ. ፩÷፲፰)

በእርግጥም ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን በመስቀል ላይ ደሙን ሲያፈስ÷ ሥጋውን ሲቆርስ የወንጀለኛ መቅጫ የሆነውን መስቀል ለእኛ ለክርስቲያኖች የሰላም አርማ÷ የጠላት ድል መንሻ በማድረጉ በሰው ልጅ ላይ ወድቆ የነበረው ኀጢአት ተሸንፏል፤ ሞት ተዋርዷል፤ ለዘመናት ሰላም አጥቶ የነበረው የሰው ልጅ ሰላሙ ተረጋግጧል፤ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ታርቋል፤ የዘለዓለም ሕይወትም ተገልጧል።

መስቀል ኀይላችን ነው!

የመስቀሉ ምሥጢር በየዓመቱ በመስከረም ወር በዓለ መስቀልን በምናከብርበት ጊዜ ብቻ የምናስበው አይደለም፤ ይልቁንም በየዕለቱ በክርስቲያናዊ ኑሮአችን ውስጥ የምንኖረው እውነታ ነው። መስቀልን ማክበር ማለት ምልክቱን በአንገት ማሰር ወይም በልብስ ላይ መጥለፍ ብቻ ሳይሆን÷ የመስቀሉን ትምህርት በሕይወታችን በተግባር መግለጥ ነው። የመስቀል ሕይወት ማለት የትሕትና ሕይወት÷ የመሥዋዕትነት ሕይወት÷ የፍቅር ሕይወትና የታዛዥነት ሕይወት መኖር ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ÷ "ማንም ሊከተለኝ ቢወድ ራሱን ይካድ፤መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ብሎ ሲያስተምረን÷ የክርስትና ሕይወት ከመስቀል ውጪ እንደማይታሰብ አስረድቶናል። በመሆኑም መስቀል ለእኛ የአንገት ላይ ጌጥ ብቻ ሳይሆን የድኅነት ምሥጢር÷ የሕይወት መንገድና የመንፈሳዊ ተጋድሎ ምልክት ነው። (ማቴ. ፲፮÷፳፬)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀል የድኅነት ምሥጢር ሲሆን፤ ያለ መስቀል ድኅነት የለም፤ ያለ ድኅነት ደግሞ ክርስትና የለም። ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን መስቀል የድኅነታችን ምልክት (አርማ)÷ የሰላማችን ምንጭ እንደሆነ ዘወትር የምታስተምረው።

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሶ ከገነት ከተባረረ በኋላ ለብዙ ዘመናት በሕይወቱ መኅሳቅል ቢደርስበትም፤ በቀራንዮ ተራራ በተሰቀለው ክርስቶስ እንደገና ወደቀደመ ክብሩና ማንነቱ ተመልሷል። በአዳም የገባውን ሞት ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ በመስቀሉ ድል አድርጎታል። የመስቀሉ ምሥጢር የእግዚአብሔር ፍቅር በተግባር የተገለጠበት ታላቅ መለኮታዊ ክስተት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ "እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋሕደ መጠወ ወወኀበ ቤዛ ለኵሉ -- በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶታልና›› በማለት የመስቀሉን መሠረታዊ ምክንያት ፍቅር መሆኑን ያስተምረናል። መስቀል የፍቅር መገለጫ ነው፤ እግዚአብሔር ፍቅሩን በቃል ብቻ አልገለጠም፤ በመስቀል ላይ ራሱን ሰጥቶ አሳይቶናል። (ዮሐ. ፫÷፲፮)

በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ሰውን ከኀጢአት÷ ከሞትና ከሰይጣን ባርነት ነፃ ያወጣ የድኅነት ሥራ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ÷ "በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ" ብሎ የተናገረው።የተቋረጠው የሰውና የእግዚአብሔር ሕብረት በመስቀሉ ታርቋልና። (ቈላስ. ፩÷፳)

ዓለም በየዘመኑ ብዙ የጠባይ ለውጦችን ብታሳይም÷ የመስቀሉ መልእክት ግን የማይለወጥ የዘለዓለም እውነት ነው። የሰው ልጅ በኀጢአት በፍርሀት÷ በብቸኝነትና በመንፈሳዊ ድካም ችግሮች ወድቆ ቆይቶ በመስቀሉ ቤዛነት ተስፋ÷ ፍቅርና ድኅነት ሊታደል በቅቷል።

የዘመናችን ትውልድ ብዙ ጊዜ ሀብትን÷ ሥልጣንንና የዓለምን ደስታ በመፈለግ የውስጥ ሰላሙን ያጣል። ነገር ግን የመስቀሉ ምሥጢር እውነተኛ ሰላም ከክርስቶስ ጋር ባለው ሕብረት ብቻ እንደሚገኝ ያስተምረናል። በመስቀሉ ላይ የተገለጠው ፍቅርም ሰውን ከራስ ወዳድነት አውጥቶ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ባልንጀራው ፍቅር ይመራዋል።

የመስቀሉ ኀይል በክርስቲያን ሕይወት የሚገለጠው በእምነት ጽናት ነው። በችግር ጊዜ ተስፋ እንዳንቆርጥ÷ በመከራ ውስጥ እግዚአብሔርን እንድንታመን÷ በፈተና ጊዜ እንድንጸና መስቀል ያስተምረናል። ምክንያቱም ከመስቀል በኋላ ትንሣኤ እንዳለ ክርስቶስ በሕይወቱ አሳይቶናል። መስቀል ለእኛ የምስክርነት ኀይል ነው።

እኛ የመስቀሉን ፍቅር በሕይወታችን ስንገልጥ÷ ለዓለም የክርስቶስ ሕያው ምስክሮች ነን። በቃላችን ብቻ ሳይሆን በተግባራችን÷ በትሕትናችን÷ በይቅርታችንና በፍቅራችን ስለ መስቀሉ ልንመሰክር ይገባናል።

ቤተ ክርስቲያን በዐለ መስቀልን ስታከብር የቀድሞውን ታሪክ አስታውሳ ብቻ ሳይሆን፤ ዛሬም በልባችን ውስጥ የመስቀሉ ሥራ እንዲቀጥል ትጠራናለች። መስቀል በቤታችን÷ በቤተሰባችን÷ በማኅበራዊ ሕይወታችንና በግል ኑሮአችን ውስጥ የፍቅርና የሰላም መርሕ እንዲሆን ታስተምረናለች።

በአጠቃላይ የመስቀሉ ምሥጢር በክርስቲያን ሕይወት የሚገለጠው÷ በእምነት÷ በፍቅር÷ በትሕትና÷ በይቅርታና በመንፈሳዊ ተጋድሎ ነው።

መስቀል የትናንት ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዛሬ ሕይወታችን መንገድ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ፍቅሩን እስከ መጨረሻ ገልጦልናል፤ እኛም ያን ፍቅር ተቀብለን በሕይወታችን ልንገልጠው ይገባናል። መስቀሉን ማክበር ማለት ከክርስቶስ ጋር መኖር ማለት ነው፤ መስቀሉን መውደድ ማለት የፍቅርን÷ የድኅነትንና የትንሣኤን መንገድ መምረጥ ማለት ነው።

እኛም ኢትዮጵያውያን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ አሳልፎ በመስጠት ያሳየንን ጥልቅ ፍቅርና ያጐናጸፈንን ድኅነት መሠረት በማድረግ፤ እርስ በርሳችን በመመካከር÷ በመከባበርና በመግባባት ፍቅርና ትሕትናን ተላብሰን ልንኖርና አልፎም ለሀገራችን መጻኢ ዕድል ማማር ልንተጋ ይጠበቅብናል።

በዐለ መስቀሉን ስናከብር ሁላችንም የመስቀሉን ምሥጢር በአእምሮአችን እንድንረዳ÷ በልባችን እንድንቀበል÷ በሕይወታችንም እንድንገልጥ የእግዚአብሔር ጸጋ አይለየን።

ልዑል እግዚአብሔር ሀገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን ይባርክ!

አባ ዲዮስቆሮስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የሪያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የማ/ማ/መምሪያና የቅ/ቅ/ጥ/ቤ/መ/ ወመዘክር መምሪያ የበላዩ ኀላፊ

መስቀል ኀይላችን ነው!

የመንፈሳዊ ዘርፍ ዋና ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት



ወበከመ ሙሴ ሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም፣ከማሁ ሃለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይሰቀል፤ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል›› (ዮሐ. 3÷14)፤

«ወበከመ ሙሴ ሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም÷ ከማሁ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይሰቀል ÷ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ÷ እንዲሁ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል›› (ዮሐ. 3÷14)። እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ ፍጹም በመሆኑ መገለባበጥና መለዋወጥ በእርሱ ዘንድ የለም፤ በሕግ÷ በፍርድና በፍትሕም በእሱ ዘንድ አድልዎ የለም። ትክክለኛ መርሕን ለፍጡራን በመስጠትም ሥነ-ፍጥረቱን ይመራል፤ ያስተዳድራልም። እሱ ከሰጠው መርሕ ያፈነገጠ ፍጡር ሲገኝም ያለ አድልዎ ይቀጣል።

ከዚህ አንጻር ከተሰጠው መርሕ ወጥቶ የተገኘው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ሕግና ፍትሕ ተፈረደበትና ተቀጣ፤ ቅጣቱ ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ሞትን ትሞታለህ በሚል ተጠቅልሎ ተገልጾአል። የሞት መሠረታዊ ትርጉም መለየት ማለት ነውና ሰው በጥፋቱ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ከገነተ ተድላ ተባረረ (ዘፍ. 3÷24)። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ በአጠቃላይ በፍርዱ መሠረት በሞት ቅጣት ሥር ወደቀ፤ የቅጣቱ ማሳያዎች÷ ሞት÷ መቃብርና ኑሮ ሁሉ በመከራ የተሞላ መሆን በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። ይህ አስፈሪ ቅጣት እስከ ስቅለተ ክርስቶስ ድረስ በሰው ልጅ ሁሉ ላይ ሰፈነ። ይሁንና ኩናኒ በርትዕ ፈታሒ በጽድቅ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ÷ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሰውን ሊታደገው እንደሆነ ለመረጣቸው ሰዎች የተስፋ ፍንጭን ሰጠ፤ ተስፋውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐላ መጣ። ከተስፋዎቹ አንዱ በእባብ ምስል ሕዝቡን ከእባብ መርዝ የታደገበትን ምሳሌያዊ አስተምህሮ ይገኝበታል።

እስራኤል በመርዛም እባቦች በተሞላ ምድረ በዳ በሚያልፉበት ጊዜ እባቦች እየነደፉ ዕልቂትን አስከተሉባቸው፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለእይታ ምቹ በሆነ ቦታ የናስ ምስል እባብን ሰቀል፤ በእባብ የተነደፈም ሁሉ እሱን ይመልከት፤ ይድናልም በማለት ለሙሴ ትእዛዝን ሰጠ፤ ሙሴም እንደ ትእዛዙ አደረገ፤ ሕዝቡም ሲነደፉ የእባቡን ምስል እያዩ ይድኑ ነበር (ዘኍ. 21÷8-9)። ይህ ምሳሌያዊ ነገር እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሰው ሊያደርገው ላሰበው ፍጹም ድኅነት ማሳያ ምሳሌ ነበር። ጌታችንም ይህንን ተስፋ ድኅነት ለሰው ልጆች ለማቀዳጀት እንደመጣ ለማረጋገጥ ይህን ምሳሌያዊ ጥቅስ ጠቅሶ አስተማረ (ዮሐ. 3÷14)። እግዚአብሔር በፍትሐዊ አሠራሩ ሰውን ለማዳን የቀየሰው መንገድ መስቀል እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ከዳር እስከ ዳር በተለያየ አገላለጽና አቀራረብ መዝግቦታል። በዚህም ዓውደ ምሥጢር መስቀል ማለት ቤዛነት ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው።

መስቀል ኀይላችን ነው!

ለኃጥኣነ እስራኤል በሙሉ ቤዛ ሆነው ይሠዉ የነበሩ በጎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍትሐዊ ፍርድ አሰጣጥን የሚያረጋግጡ ነበሩ (ዘሌ. 4÷32-35)። እግዚአብሔር ሰውን የሚያድነው የቀደመውን ፍርድ በዘፈቀደ ሰርዞ ሳይሆን፥ ፍርዱም ምሕረቱም እንደተከበረ ይቅርታ የሚሰጥበትን አሠራር በመቀየስ እንደሆነ አሳየ (ሮሜ 3÷21-26)፤ ይኸውም የሚሆነው የተፈረደውን የሞት ፍርድ ሊቀበል የሚችል ሌላ አካል ስለ ሰው ነጢአት ቤዛ ሆኖ እንዲሞት ማድረግና በዚህ ፍርዱ ሳይቀለበስ እንዳለ እንዲፈጸም ማስቻል፤ የፍርዱ ተሸካሚ የነበሩ ሰዎችም በእነሱ ፈንታ ሌላ አካል ስለ ሞተላቸው ከፍርዱ ነጻ ሆነው እንዲለቀቁ ማስቻል ነው።

እግዚአብሔር ይህንን ፍትሐዊና ከእውነት ጋር የማይጋጭ የዳኝነት አሠራርን ተጠቅሞ ሰውን ከሞት ለማዳን ፈቃዱ ሆነ፤ ይህንንም ፈቃዱን በኦሪት፥ በመዝሙራትና በነቢያት ሲገልጽ ከቁየ በኋላ፥ የሰው ሁሉ ቤዛ ሆኖ የሚሠዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሥዋዕት የሚሆን ሰውነታችንን ነሥቶ በዚህ ዓለም ተገለጸ፤ የቤዛነት ሥራውንም በብዙ ጎብረ አምላል እየገለጸ ለተከታዮቹ አሠረጸ (ዕብ. 9÷22)። ከቤዛዊ ትምህርቱም አንዱ የሙሴን እባብ ጠቅሶ፥ የእሱን መሰቀል አስፈላጊነትና ግድነት ያስተማረበት ይገኝበታል።

ከላይ በተገለጸው የእግዚአብሔር አሠራር መሠረት ያለ ደም ስርየት አይገኝምና የእሱን መሰቀል የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ጌታችን አስረግጦ በተደጋጋሚ አስተምሮአል፤ ይህንን ለመቃወም የሞከሩትንም አጥብቆ ገሥጾአል (ማቴ. 16÷21-23)። ጌታችን የእሱን መሰቀል አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ሲያብራራ፥ በእሱ የሚያምን ሁሉ ከጥፋት እንዲድን እንደሆነ አሳይቶአል። የእግዚአብሔር ሕግ በነጢአተኛ ላይ ሲፈርድ ሰውን ለከባድ ጥፋት ይዳርጋል፤ በመሆኑም ሰው በዚህ ምክንያት በሚያጠፋ ፍርድ ሥር ውሎአል። ሰው ከደረሰበት ጥፋት መዳን የሚችለው በእሱ ፈንታ ቤዛ ሆኖ የሚሞት ሲገኝ ብቻ ስለሆነ ለዚህ ሲባል የጌታችን መሰቀል ግድ እንደሆነ ጌታችን በግልጽ አሳወቀ፤ በተግባርም ያንኑ ፈጸመ። በዚህ ምክንያት ሰዎች ከጥፋት ወጥተን ምሕረትን የምናገኝበት ዕድል ተፈጥሮልናል።

ዛሬ እግዚአብሔር እኛን ይቅር ብሎ የሚቀበልበትን አሠራር ዘርግቶአል፤ እሱም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባደረገው የማዳን ሥራ ማመን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ስናምን የእሱን ጽድቅ ለእኛ ይቁጠርልናል (ሮሜ 4÷25)። የእሱ ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ስለሆነ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነውን የእሱን ጽድቅ ለእኛ ይቁጥርልንና በእሱ ከጥፋት አምልጠን እንድናለን። ‹‹በእኔ የሚያምን ሞትን አይቀምስም (ዮሐ. 8÷51፡52)፤ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም›› (ዮሐ. 14÷6) በማለት እቅጩን የነገረንም ለዚህ ነው።

መሰቀል ወይም ተሰቅሎ ኀይላችን ነው፤ ጽናታችን ነው፤ ቤዛችን ነው፤ የነፍሳችን መዳኛ ነው የምንለው የሚያድነን በስቅለቱ ጊዜ የተፈጸመው ቤዛዊ መሥዋዕት እንጂ ሌላ ባለመኖሩ ነው። ይህ ቤዛዊ መሥዋዕት የተሠዋበት ዕፀ መስቀልም ቅዱስ መሠዊያ ነውና፤ መሥዋዕቱንና በመሥዋዕቱ የተገኘውን ድኅነታችንን የምናይበት፥ የምናስብበትና የምናስታውስበት ወደር የሌለው የድኅነት አርማችን ነው። ስለሆነም በቤተ ክርስቲያናችን ጉልላት ሁሉ ከፍ ብሎ ይቀመጣል፤ በዚያም ሆኖ ድኅነተ ዓለምን በመንገር፥ በመመስከርና በማወጅ ሰው ሁሉ በክርስቶስ ጽድቅ ጻድቅ እንዲሆን ይጠራል።

ዕፀ መስቀል ክርስቶስን፥ መሥዋዕትነቱንና አዳኝነቱን የወከለ ስለሆነ፥ እሱን ስንሳለም በመንፈስ ክርስቶስን እንሳለማለን፤ ከመስቀሉ በስተጀርባ ባለ ክርስቶስም እንባረካለን። ታድያ ይህንን ሁሉ መልእክት የተሸከመ ዕፀ መስቀል ተቀብሮ እንዲቀር የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረምና፥ በልዩ አጠራሩ ንግሥት ዕሌኒን አነግሥቶ ከተቀበረበት ጉድጓድ እንዲወጣ አድርጎአል። እግዚአብሔር ይህንን ሲያደርግ ምን ማለቱ እንደሆነ ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ግልጽ ነበር፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንዲ ብቻ ሳትሆን የመጀመሪያዋ ስለሆነች የዕፀ መስቀሉን ክብርና በተሰቅሎው የተገኘ የመዳናችንን ምሥጢር አጥብቃ ይዛ እምነቷን በማስፋፋትና በማሻገር ትገኛለች።

አዲሱ ትውልድም ከመጀመሪያው ዘመን አንሥቶ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ቋንቋቸው ተርጕመው ከተገኙ ጥቂት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዲ መሆኗን፥ የራሷ የሆነው የግእዝ ቋንቋን፥ ሄኖሳዊ የሆነው ፊደሏን፥ ኖኃዊ የሆነው የዘመን አቈጣጠርዋን እስካሁን ጠብቃ ያቈየች የብቸኛዋ ብርቅዬ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት መሆኑን ተገንዝቡ፥ በሁሉም ነገር ቤተ ክርስቲያኑን ከጥቃትና ከፍልሰት ነቅቶ እንዲጠብቅ ከእግዚአብሔርም፥ ከአበውም፥ ከታሪክም አደራ ተጥሎበታል፤ በዓለ መስቀልን የማክበር ተልእኮው ይህ ነውና።

ወለእግዚአብሔር ኣኰቴት

ዘወሀብነ ንማዕ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት

የመንፈሳዊ ዘርፍ ዋና ምክትል ስራ አስኪያጅ



የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፉ ዋና ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት

«ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ»

«ወእንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜኅር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ፥ ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።»

(ገላትያ 6፥14)

መስቀል ኀይላችን ነው!

እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ፤ አደረሰን።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች በላከው መልእክቱ እንደተናገረው፦ የክርስቲያኖች እውነተኛ ትምክህት፥ ድኅነትና የክብር አክሊል በመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅዱስ መስቀሉ ነው። መስቀል በብሉይ ኪዳን የመረገምና የውርደት ምልክት የነበረ ሲሆን፥ የጌታችን ቅዱስ አካሉ በተቸነከረበትና መለኮታዊ ደሙ በፈሰሰበት ዕለት ግን የሕይወት መሠረት፥ የዕርቅ ምልክት የዲያብሎስ ድል መንሻ ኀይል ሆኗል። መስቀል የክርስቶስ ፍቅር እስከ ሞት ድረስ የተገለጠበት አምላካዊ መድረክ ነው።

እኛም ዛሬ እንደ ክርስቲያን የምንመካው በዓለማዊ ነገሮች ሳይሆን፥ እግዚአብሔርና ሰዎችን፥ ሰማይንና ምድርን፥ ሕዝብና አሕዛብን ባስታረቀው መስቀሉ ሊሆን ይገባል። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ስለ መስቀሉ የማዳን ምሥጢር ሲያስተምር፦ «ክርስቶስ እጆቹን በመስቀል ላይ የዘረጋው ሁለቱን ሕዝቦች (አይሁድና አሕዛብን) ለማቀፍና ምድርን ከሰማይ ጋር ለማያያዝ ነው፤ በመስቀሉ በምድርና በሰማይ መካከል የተሰቀለውም ዲያብሎስን ለማውረድና ሰማያዊ መንገዳችንን ለማጽዳት ነው» (ቅዱስ አትናቴዎስ፥ በእንተ ተሰግዎቱ ለቃል፥ አንቀጽ 25) ይላል።

የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራ ያለው ጉዳይ ነው። በዐራተኛው ክፍለ ዘመን ንግሥት ዕሌኒ የጌታችንን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት በፈለገች ጊዜ የደመራ ጢስ አቅጣጫ እንደመራት ሁሉ፥ በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የምናከብረው የመስቀል ደመራ በዓል ይህን ታሪካዊና መንፈሳዊ እውነት ያሳስበናል። በተለይም ደግሞ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ያደረጉት ታሪካዊና መንፈሳዊ ተጋድሎ ፍሬ አፍርቶ፥ የጌታችን ግማደ መስቀል ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከገባበት ዕለትና በግሸን ደብረ ከርቤ ገዳም ካረፈበት ጊዜ ጀምሮ፥ በዓሉ በሀገራችን በታላቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት ሲከበር ቆይቷል።

የመስቀል ደመራም ምድር በአበቦች በምታጌጥበት፥ የክረምት ማለፍ ቀርቦ የፍሬ በረከት ዘመን በሚመጣበት የተስፋ ወቅት መስከረም ወር ላይ ተደምሮ የሚከበር ሃይማኖታዊ ምሥጢሩ የጎላ ልዩ በዓል ነው። የበዓሉ ሥርዓትና ታሪካዊ ዕሴት በዩኔስኮ (UNESCO) የማይጨበጥ የዓለም ቅርስ ሆኖ መመዝገቡ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ሀገራዊ ዕሴቷን ጠብቃ ለዓለም ያበረከተችው ታላቅ ሀብት መሆኑን ያሳያል። ይህ በዓል ለኢትዮጵያ የታሪካዊነት፥ የትውፊታዊ ቅርስ ባለጠግነት፥ ያልተቋረጠ ሥርዓተ መንግሥት ባለቤትነት ሁሉ ምስክርና ምልክት ነው። መስቀልና ከመስቀል ጋር የተገናኙ ነገሮች ሁሉ የአጋጣሚና የጊዜያዊ ፍላጎት ውጤቶች ሳይሆኑ የሰላምና የዕርቅ መሻትና የሀገራዊ አንድነት ተጋድሎ የወለዳቸው ናቸው። ስለዚህ ሃይማኖትን ማክበር፥ ታሪክን መጠበቅ፥ ከፉክክር መንፈስ ወጥቶ ታሪካዊ ሥራ መሥራትና መጠሪያ ማግኘት ያስፈልጋል።

በጌታችን መስቀል የአምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን የሰው ልጆች ሰቆቃና መከራ ተወግዷልና፥ አሁንም መስቀል ለምንሰጋቸው ጉዳዮች ሁሉ መትረፊያ የሚሆን ትምክሕት ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ፦ “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፥ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ» (ገላትያ 6፥14) ያለው። ስለዚህ የመስቀልን በዓል በምናከብርበት ጊዜ በመስቀሉ ሰላምን እናውጅ፥ በመስቀሉ የጥልን ግድግዳ እናፍርስ፥ በመስቀሉ ለሰዎች ሕይወት የሚሆነውን ብቻ በማሰብና በመሥራት ምስክሮች እንሁን።

ረዳት ፕሮፌሰር ቀሲስ ግርማ ባቱ

በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ





"ዘኢጸረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ይጸመደኒ ÷ መስቀሌኒ ሊሸከም የማይወድ ሊከተለኝ አይችልም።"

(ሉቃ. 14÷27)

በሊቀ ማእምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ
የሊቃውንት ጉባኤ አባልና የሚድያና ኮሚዩኒኬሽን ክፍል ኀላፊ

የቅዱስ መስቀል በዓል በዝማሬና በደስታ መንፈስ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በየዓመቱ መከበሩ ዋንኛ ምክንያት የመስቀሉ ድል አድራጊነት ነው። በመጀመሪያ መስቀል የወንጀለኞች ቅጣት መፈጸሚያ ነበር። የሰው ልጅ የአምላክን ፈቃድ በመተላለፉ ከደረሰበት ውድቀት እንዲድን እግዚአብሔር ወልድ ውድቀቱን ወደ ትንሣኤ፥ ሐሣሩን ወደ ክብር ሊቀይረው በመስቀል ላይ ተሰቀለ። በመስቀሉ የተሻረው በሰው ልጅ ላይ የደረሰው ውድቀትና ውርደት ይልቁንም ዘለዓለማዊ ሞቱ ነው።

ስለዚህም በመስቀል ላይ በተፈጸመው መለኮታዊ የማዳን ተግባር ሞት ድል ተደርጓል፤ ስለዚህም በዓለም ላይ ላለን ክርስቲያኖች ሁሉ መስቀል የድል አድራጊነት ምልክታችን ነው። መስቀል የድል ምልክትና አርማ የሆነው ግን ጌታችን አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው መከራ መስቀል እንጂ መስቀል የውርደት ምልክት ነበር። ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ካሳየው የትሕትና ማሳያዎች አንዱ በመስቀል እስከ መሰቀል ድረስ መፍቀዱ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል። (ፊልጵ. 2÷8)

መስቀል በሮማውያን ዘንድ ከነበረው የመቅጫነት እሳቤ የተነሣ የውርደትና የወንጀለኛነት ምልክት እንደነበረ ሁሉ፥ አሁንም ለማያምኑ ሞኝነት ነው። በክርስቶስ ለምናምን በዓለም ዙሪያ ለምንኖር ሁሉ ግን መስቀል ኀይላችን ነው፤ መስቀል ጽንዓችን ነው፤ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው (1ኛ ቆሮ. 2÷14)። መስቀል ኀይልና ጽንዕ የሚሆነው የዘለዓለም ሕይወትን ስለሚያስገኝ ነው፤ በዓለም ላለን ክርስቲያንም የምኞት ምልክት አይደለም። ስለ መስቀል ደጋግሞ የጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቅዱስ መስቀል ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንም እንደማይመካ ከገለጸ በኋላ "ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተ፥ እኔም በዓለሙ ዘንድ የሞትኩ ነኝና" ሲል በገላትያ መልእክቱ ላይ መግለጹ ዓለማዊ ምኞትና መስቀል አብረው የማይገኙ መሆናቸውን ያሳያል። (ገላ. 6÷14)

ክርስቲያኖች በመስቀሉ የድል አድራጊ ምልክትነት አምነው ሲኖሩ በክርስትናቸው ምክንያት የሚደርስባቸው ምድራዊ ፈተናም የሚመሰለው በመስቀል ነው። አምላካችን ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ካስተማራቸው የጸኑ

መስቀል ኀይላችን ነው!

ትምህርቶች አንዱ ክርስትና የዘለዓለማዊ ሕይወት እንጂ የምድራዊ ምቾት ምልክት አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡ ፡ “መስቀሌን ሊሸከም የማይወድ ሊከተለኝ አይችልም” (ሉቃ. 14÷27)። መስቀል ክርስቲያኖች ክርስቶስን በቁርጠኝነት የመከተላችን፥ መከራንም የመጋፈጣችን ምልክት ነው። ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፤ የሞቱንም መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ። (ማቴ. 16÷24)

በክርስቶስ ያመንን ሁሉ መስቀል ከክርስቶስ ጋር የምንመሳሰልበት ትእምርት እንደሆነ እናምናለን። በመከራው (በመስቀሉ) እንደምንመስለው ሁሉ፥ በድል አድራጊነቱም እንመስለዋለን። በመስቀሉ የምድርንም የሲኦልንም ኀይላት ድል እናደርጋለን። በአንጻሩ የማያምኑ በመስቀሉ ደጋግመው ድል ይደረጋሉ። ደጋግመውም መስቀሉን ይቃወሙታል። መስቀሉ ግን የዘለዓለማዊ ድል አድራጊነትና የፍጹም ፍቅር ምልክት ነው። አምላክ ሰውን ከመውደዱ የተነሣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የማዳን ሥራውን አከናውኗል። በመስቀሉ ዛሬም፥ እስከ ዘለዓለምም ድረስ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ይገለጻል፤ የታመሙ ይድናሉ፥ ለምጻሞች ይነጻሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ። ጌታችን አምላክችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል በርካቶች ከሞት ወደ ሕይወት መነሣታቸውን ድርሳናት ያስረዳሉ። በመስቀሉ ያመኑ ከደዌና ሞት እንደሚድኑ ሁሉ፥ በምድር ኀያላን ፊት ክስና ወቀሳ፥ ከዛም ከፍ ሲል የመረረ ቅጣት እየተቀበሉ እስከ ዛሬ ድረስ አሉ።

ክርስቲያኖች በክርስቶስ ሞት ያገኘነውን የልጅነት ጸጋ እንድንወርስ በመስቀል ልንመስለው የግድ ስለሆነ፥ በዓለም ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ ሃይማኖታቸው ሥቃይና መከራን እየተቀበሉ ይገኛሉ።

የዘመናችን መስቀል በክርስቲያኖች ሕይወት

ክርስቲያኖች በብዙ የዓለም ክፍሎች በእምነታቸው ምክንያት ብዙ ግፍ ይደርስባቸዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የእምነት ነፃነትና የሃይማኖት እኩልነትን የሚያቀነቅኑ ሰዎች ክርስቲያኖች ቢሆኑም፥ ዛሬም የመስቀሉ መከራ ከክርስቲያኖች ጫንቃ አልወረደም። ክርስቲያኖች በብዙ የዓለም ክፍሎች በመንግሥታት፥ በተቋማትና በማኅበረሰቦች ይገፋሉ። እንደ ሰሜን ኮሪያ በመሳሰሉ ሀገራት መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ መገኘት በሞት ወይም አስከፊ በሆነ የጉልበት ሥራ ያስቀጣል። ኡዝቤክስታን የተባለችው ሀገር ያልተፈቀደ የሃይማኖት መጽሐፍ መያዝን የሚከለክል ሕግ በቅርብ አውጥታለች፤ ይህም ክርስትናን የሚከለክል ሕግ ነው።

በአንዳንድ ሀገራት መንግሥት በፈቀዳቸው ሥፍራዎች ካልሆነ የአምልኮ ሥርዓት መፈጸም ይከለከላል። አብያተ ክርስቲያናት ይቃጠላሉ። ካህናትና ምእመናን ይገደላሉ። በማኅበረሰቦችና የጋራ በሆኑ ተቋማት ሞትና መገለል ሲደርስባቸው እንኳን ሞታቸውና መከራቸው ዕውቅና አይሰጠውም። በብዙ የዓለም አካባቢዎች ክርስቲያኖችን መጨቆን ሌሎችን እኩል እንደማድረግ ተደርጎ ይቆጠራል። የእርሻ ማሳቸው ይቃጠላል፤ እንስሳቶቻቸው ይዘረፋሉ፤ ሴቶች ይደፈራሉ፤ በጎይል የሌላ እምነት ተከታዮች ወንዶችን እንዲያገቡ ይደረጋል፤ ሃይማታቸውን እንዲቀይሩ ይገደዳሉ፤ የኢኮኖሚ ነፃነት ይከለከላሉ። በሕይወት ለመቆየትና ሠርቶ ለመኖር ሲሉ ሃይማታቸውን በቀጣሪዎቻቸው እንዲቀይሩ ይደረጋሉ። ሃይማኖትን ለማስፋፋትና ክርስቲያኖች ላይ የኢኮኖሚ የበላይነት ለማግኘት ሲባል ከሀገራት ዓመታዊ በጀት ጋር የሚፎካከር የገንዘብ መጠን ፈሰስ ይደረጋል። አንዳንድ ሀገራት አግላይና በዳይ ሕግጋትን ያወጣሉ። እንደ ፓኪስታን ያሉ ሀገራት ክርስትናን መቀበል እስልምናን እንደ መስደብ የሚቈጥሩ ሕጎችን ያወጣሉ፤ ይተገብራሉ። ክርስቲያኖች በሕግም በደቦ ፍርድም ይገደላሉ፤ በዘፈቀደ ይታሰራሉ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በኦቶማን ቱርኮች በአርመን ኦርቶዶክሳውያን ከተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ጀምሮ እስካሁን ድረስ ስልታዊ ጭቆና በአርመን ክርስቶሳውያን ላይ ይደርሳል። በመካከለኛው ምሥራቅ በክርስቲያኖች ላይ ከደረሰው አስከፊና ተከታታይ ጭፍጨፋ የተነሣ የአማንያን ቍጥር ከዐሥር እስከ ዐሥራ ሁለት ሚሊዮን በሚያህል ቍጥራቸው መቀነሱን ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ያስረዳሉ። World Christian Data Base የተባለው ማዕከል Status of Global Christianity, 2026 in the context of 1900-2075 በሚላ ባቀረበው ጥናት የመካከለኛው ምሥራቅ አማኞች በፍጥነት መመናመንን ምክንያቶች ዘርዝሯል። Pew Research የተባለው ሌላ የጥናት ተቋምም Christian Churches and ArabChristians in the Hashemite Kingdom of Jordan በሚል ባሳተመው ጥናት ይህንን አረጋግጧል።

ከአፍሪካ ናይጄሪያ፥ አልጄሪያ፥ ቱኒዝያ፥ ሊቢያና ሶማሊያ የክርስቲያኖች የሥቃይ ማእከላት መሆናቸውን ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ያሳያሉ። ከመካከለኛው ምሥራቅ ሊቢያ፥ ሶርያ፥ ኢራንና የመሳሰሉ ሀገራት የክርስቲያን የሥቃይ ሀገራት መሆናቸው ሲታወቅ፤ እንደ ፓኪስታን የመሳሰሉ የእስያ ሀገራትም ለክርስቲያኖች የምድር ላይ ሲኦል ሆነዋል። በኢትዮጵያችን በርካታ አብያተ ክርስቲያን የሚቃጠሉ፥ በርካታ አማንያንን የሚገደሉ፥ በአስገዳጅ ሁኔታ ሃይማኖታቸውን እንዲቀይሩ የሚገደዱ ቢሆንም እንኳ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚወጡ ሪፖርች አለመካተቱ በሌሎች አካባቢዎች የሚፈጸመው ፀረ-ክርስትና ተግባር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

መስቀል ኀይላችን ነው!

አንዳንድ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመው የዘር ማጽዳት ጭፍጨፋ ክርስቲያኖችን ወደ መጥፋት ደረጃ እያደረሰ ነው። በኢራቅ እኤአ በ2011 ዓ.ም. አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የነበረው የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ቁጥር በ2024 ዓ.ም. ወደ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ማሽቆልቆሉን፤ በሶሪያ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የነበረው የክርስቲያኖች ቁጥር በተፈጸመባቸው ጭፍጨፋ በ2024 ወደ ሦስት መቶ ሺህ መድረሱን የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪፖርት ያመለክታል። ባግዳድና ባዝራን የመሳሰሉ የኢራቅ ከተሞች ሙሉ በሙሉ ክርስቲያኖች ነፃ መሆናቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ።

በክርስትናው ላይ የመስቀል መከራ እንዲጸና ከሚያደርጉ ምክንያቶች ዋነኞቹ ሃይማኖታዊ መንግሥታትና ታጣቂ የሃይማኖት ንቅናቄዎች ናቸው። እንደ ግብፅ ያሉ ሀገራት በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርጉት የፖሊሲና የኢኮኖሚ ተጽዕኖ ክርስቲያኖች ከሀገራቸው እንዲሰደዱ ያደርጋቸዋል። በአንዳንድ ሀገራት ደግሞ ክርስትናን ከተቀበሉ በሌላ ሃይማኖት ላይ ጥቃት እንዳደረሱ የሚቈጥሩ ሕጎች መኖራቸው ጥቃቱን ከባድ አድርጎታል።

የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ግድያ አልፎ አልፎ በግጭት ምክንያት የሚከሠት ሳይሆን የዕለት ዕለት ክሥተት ነው። በ2025 ዓ.ም. የወጡ ዘገባዎች እስከ አምስት ሺህ የሚደርሱ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ምክንያት እንደተገደሉ የዘገቡ ሲሆን፤ ይህም በየቀኑ ዐሥራ ሦስት ክርስቲያኖች በአማካይ እንደሚገደሉ ያሳያል። ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑ ፀረ-ክርስትና ግድያዎች ከሰሀራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ይፈጸማሉ። ከእነዚህ መካከል ከሰባ በመቶ በላይ የሚሆነው የክርስቲያኖች ግድያ በናይጄሪያ እንደ ቦኮሀራም ባሉ ጽንፈኛ ቡድኖች እንደሚፈጸሙ Open Doors International እና Holy See's Permanent Observer to the United Nations የተባሉ ገለልተኛ የጥናት ተቋማት ያወጧቸው ሪፖርቶች ያስረዳሉ። እነዚህ ዓለም አቀፍ ቁጥሮች በሃይማታቸው ምክንያት የሚገደሉ ክርስቲያኖችን በሙሉ እንደማያሳዩ ግልጽ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚፈጸሙት ግድያዎች አለመጠቀሳቸው በርከት ያሉ ቁጥሮች የሪፖርቶቹና የጥናቶቹ አካላት እንዳልሆኑ ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። አሁንም የመስቀሉ መከራ በዓለም ክርስቲያኖች ይልቁንም በኦርቶዶክሳውያን ላይ እየከበደና ከጊዜ ወደ ጊዜም እየባሰ በመሄድ ላይ ነው። የዓለም ክርስቲያኖችም መስቀሉን ተሸክመው ክርስቶስን በመከተል ስማዕትነትን በመቀበል ላይ ናቸው።

የመስቀልን በዓል በምናከብርበት በዚህ አጋጣሚ በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ በመስቀል ምክንያት እየደረሰ ያለውን መከራ በማሰብ የመስቀሉንም ተስፋ በመጠባበቅ ሊሆን ይገባል።

«መስቀሌን ሊሸከም የማይወድ ሊከተለኝ አይችልም» በሚለውን ቃለ ወንጌል አምነው በሰማዕትነት የሚያልፉ ቅዱሳን በረከት ይደርብን።

ምንጭ

1. Holy See's Permanent Observer to the United Nations, http/www.vaticannews.va/en/Vatican-city/new/2026-03/holy-see-christian-persecution-relogious-freedom-human-rights.html
2. Mark Hearly Bonner, Jane AdolpheEtal, 2017. The Persecution and Genocide of Christians in the Middle East. Maria School of Law, Angelico Press,2017
3. Open Doors International. http/www.opendoors.org.hg/en-us/news/latest/ww/2026-overview/.
4. World Watch List 2026 Overview,14-1-2026,
5. WORLD: 2026 Annual Report of the United States Commission on International Religious Freedom
6. Paolo Maggiolini, 2015. Christian Churches and ArabChristians in the HashemiteKingdom of Jordan : Citizenship, Ecclesiastical Identity and Roles in the Jordanian Political Field, On Open Editions Journal
7. worldchristiandatabase.org, 2026. Status of Global Christianity, 2026, in the Context of 1900—2075 World Christian Data Base.

መስቀል ኀይላችን ነው!



"እንሰ ሐሰ ለተ ኢይዜነር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ÷ አጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ለእኔ ይሩቅ።"

(ገላ. 6÷14)

በመልአከ አሚን አባ ላእከ ማርያም ገብረ ጊዮርጊስ (ቆሞስ)
የሊቃውንት ጉባኤ አባልና የዕቅበተ ሃይማኖት ዘርፍ ክፍል ኀላፊ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቲያናዊ ሕይወትን ፍጻሜና ማጠቃለያ በዚህ አጭር ኀይለ ቃል ይገልጠዋል፤ በአይሁድ ሕግ ዘንድ የተረገመ (ዘዳ. 21÷23)፥ በሮማውያን ሥርዐት ዘንድም የውርደት ምልክት የነበረውን መስቀል፦ "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፥ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" በማለት የዘለዓለም ክብርና ብቸኛ ትምክሕቱ አድርጎ ያቀርበዋል። ይህ ትምክሕት በከንቱ ውዳሴና በትዕቢት የሚገለጥ ሳይሆን፥ ክርስቲያን ከኀጢአተኛው ዓለም ፈቃድና ምኞት ፍጹም ተለይቶ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስበት፥ ዕለት ዕለት የሚሞትበትና ከክርስቶስ ጋር ሕያው ሆኖ የሚነሣበት የምሥጢረ ድኅነት ማእከል ነው።

ነገረ መስቀል

ነገረ መስቀል ማለት የሰው ልጅን ከአበሳውና ከዘለዓለም ሞት ለማዳን የተገለጠው መለኮታዊ ፍቅር፥ ጥበብና ምሥጢር የሚነገርበት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ክርስቲያን የነገረ ድኅነት ትምህርት ዋና መሠረትና ማእከል ነው። መስቀል በጥንት ዘመን የውርደት፥ የሕመም፥ የምሬትና የጽኑ መቅሠፍት ምልክት የነበረ ቢሆንም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በላዩ ላይ በመሰቀሉ ምክንያት፦ የድል፥ የሕይወት፥ የሰላምና የመዳናችን አርማ ሆኗል።

ሀ. የመስቀሉ ቃል የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ ነገረ መስቀሉሰ እበድ ውእቱ በኀበ ኀጕላን ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ፤ የመስቀሉ ነገር በሚጠፉ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ነው፤ ለምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው" (1ኛ ቆሮ. 1÷18) በማለት እንደገለጸው፥ የነገረ መስቀል ምሥጢር በሰው ልጅ ውስን አእምሮና በፍልስፍና ሚዛን ተመዝኖ የሚደረስበት አይደለም።

በመሆኑም ለዚህ ዓለም ጥበበኞች "ስለ እኛ በፈቃዱ ሰው የሆነው ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔር ለዓለም ድኅነት ሲል በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በሥጋ ሞተ" የሚለው ሐሳብ የሞኝነትና የድካም አመለካከት መስሎ ይታያቸዋል። በክርስቶስ ክርስቲያን ለተሰኘን ለእኛ ለምእመናን ግን መስቀል የእግዚአብሔር ኀይል፥ የዲያብሎስ ድል መነሻና የሰው ልጅ ከኀጢአት እስራት ነፃ የወጣበት ታላቁ የመዳን ኀይል ነው። ሰው በኀጢአቱ ከፈጣሪው ጋር በመጣላቱ ምክንያት ከምድር ወደ ሰማይ የሚደርሰው የሰላምና የይቅርታ መንገድ ተዘግቶ ነበር።

ነገር ግን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቈላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ፦ "ወቦቱ ይሣሀሎ ለኵሉ ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበሰማይ ወለዘበምድር፤ ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀሉ ባፈሰሰው ደም በሰማይና በምድር ላሉት ሁሉ ሰላምን አደረገ" (ቈላስ. 1÷20) በማለት እንደገለጸው፥ እግዚአብሔር ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታረቀው በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ቅዱስ ደሙ ነው። በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሷል፤ በሰማያውያንና በምድራውያን መካከል ታላቅ ሰላምና አንድነት ተመሠርቷል፤ እንዲሁም የኀጢአት ዕዳችን በሙሉ ተደምስሷል። (ቈላስ. 2÷14)

መስቀል ኀይላችን ነው!

ሀ. ጌታችን እጆቹን ዘርግቶ ሕዝብና አሕዛብን ወደ እርሱ ያሰበሰበው በመስቀል ነው፤

ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን አባት ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ "በእንተ ሥጋዌሁ ለቃለ እግዚአብሔር፤ ስለ እግዚአብሔር ቃል ሰው መሆን" በተሰኘው መጽሐፉ ምዕራፍ 25 ላይ የክርስቶስን በመስቀል ላይ እጆቹን መዘርጋት ምሥጢር ሲያበራራ፦ "ክርስቶስ በአየር ላይ የተዘረጉትን የአጋንንት ኀይላት ለመደምሰስና ወደ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ሊከፍትልን ሁለቱ እጆቹን በመስቀል ላይ ዘረጋ" ይላል። ይኸውም ሰይጣን በአየር ላይ ሰልፍ አዘጋጅቶ የሰውን ልጅ ወደ ሰማያዊው ቤት እንዳይገባ ይከለክል ስለነበር፥ ክርስቶስ በአየር ላይ በመስቀል ተሰቅሎ እጆቹን በመዘርጋት የአጋንንትን ኀይል ደመሰሰልን፤ የሰውንም ልጅ በሙሉ ወደ እቅፉ በመጥራትና የተከለከለውን ሰማያዊውን መንገድ በመክፈት ወደ እርሱ አቅርቦናል።

እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ ፍጡር መክፈል ያልቻለውን የኀጢአት ዕዳ ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በመስቀል ላይ በመሞት ከፈለልን። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፥ እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" (ገላ. 6÷14) እንዳለ፥ መስቀል ለምእመናን ሁሉ የድል፥ የሕይወትና የዘለዓለም ድኅነት ምክር ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ ከዚህ ከክርስቶስ መስቀልና ከፍቅሩ ውጭ ሌላ የድኅነት ትምክሕት ሊኖረው አይችልም።

ቅዱስ መስቀል (ዕፀ መስቀል)

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው የተቸነከረበትና ክቡር ደሙ የፈሰሰበት ያ ግዙፍ ዕፅ (ቅዱስ መስቀል)፥ በጌታ ሕማማትና ሞት ምክንያት የቅድስና፥ የበረከት፥ የኀይልና የፈውስ ምንጭ ሆኗል። በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ በወንጀሉ ምክንያት የሚቀጣበትና የእርግማን ምልክት የነበረው መስቀል፥ በክርስቶስ ደም ቅድስናን አግኝቶ ምእመናን ጥንተ ጠላታቸው ዲያብሎስን የሚያሸንፉበት የድል አርማ ሆኗል።

ሀ. ከሕግ እርግማን የመዋጀት ምሥጢር፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ የኦሪትን ሕግና የመስቀሉን ነገር ሲያነጻጽር፦ "ወለነሰ ተሣየጠነ ክርስቶስ እመርገማ ለኦሪት በዘወድአ በእንቲአነ ወፆረ መርገማ፤ እኛንስ ክርስቶስ ስለ እኛ የኦሪትን መርገም በመሸከሙ ከኦሪት መርገም ዋጅቶናል""(ገላ. 3÷13)። "ከመዝ ይቤ መጽሐፍ ርጉም ውእቱ ኵሉ ዘስቀል ዲበ ዕፅ፤ በዕንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ ርጉም ነው ተብሎ ተጽፎአልና" እንዳለ። በኦሪት ሕግ መሠረት በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሰው የተረገመ ይባል ነበር (ዘዳ. 21÷23)፤ ነገር ግን እርሱ በዘለዓለማዊው ህላዌው ፍጹም ንጹሕ ሆኖ የሚኖር ቅዱስ አምላክ ሲሆን፤ ስለ እኛ ሲል የኦሪትን እርግማን በመሸከሙ፥ እኛን ከነበረብን የሕግ እርግማንና የዘለዓለም ሞት ነፃ አወጣን፤ እርግማኑንም ወደ በረከት ለወጠልን።

ለ. ዕፀ በለስና ዕፀ መስቀል፤

በዕፀ በለስ አማካኝነት ያጣነውን ልጅነት በድጋሚ ገንዘብ ያደረግነው በመስቀሉ ባገኘነው በረከት ነው፤ ወይም ቀድሞ ሰዎች በዕፅ ምክንያት ከገነት እንደተባረርን ሁሉ፥ በኋላም ወደ ቦታችን ወደ ገነትና ወደ ርስተ መንግሥተ ሰማያት የተመለስነው በዕፅ ምክንያት ነው። ይህንን ምሥጢር ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖተ አበው፦ "ቃላ ለሔዋን ከሠተ ዕፀ፤ የሔዋን ልብላ ልብላ ማለቷ፥ ዕፀ በለስ የሞት ምክንያት ሆነ"፤ "ወበውእቱ ዕፅ ወፅአ አዳም እመገነተ ተድላ፤ በዚያም ዕፅ አዳም ተድላ ደስታ ካለበት ከገነት ወጣ"፤ "ወቃልሰ ዘተወልደ እምድንግል ከሠተ መስቀለ1፤ ከድንግል የተወለደ አካላዊ ቃል ግን መስቀል የድኅነት ምክንያት እንደሆነ ገለጠ"፤ "ወቦቱ ቦአ ፈያታዊ ውስተ ገነተ ተድላ ዘምስለ አቡሁ አዳም ወሰሎሞ፡ አበው ቀደምት፤ በዚያም መስቀል ቀማኛ፥ ወንበዴ የነበረው ሰው ከአባቱ ከአዳምና ከቀደሙ አባቶች ሁሉ ጋር ተድላ ደስታ ወዳለበት ገነት ገባ" በማለት ይገልጻል። (ሃይ.አበ. ምዕ. 67፥ ክፍል 11፥ ቁጥር 5)

ይህ በሁለቱ ዕፀዋት ንጽጽር መነሻውን ያደረገ የሊቁ አስተምህሮ፥ የመጀመሪያዋ ዕፅ (ዕፀ በለስ) የሞት ምክንያት እንደሆነችና በእርሷም ምክንያት አዳም ተድላ ደስታ ካለበት ከገነት እንደተባረረ ሁሉ፥ ከድንግል ማርያም የተወለደው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞቱ መስቀሉ የመዳን ምክንያት እንደሆነና በመስቀሉ ላይ በተገለጠው ምሕረትም፥ በቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ "አቤቱ በመንግሥትህ አስበኝ" ባለው ጊዜ፥ ከአዳምና ከቀደሙት አባቶች ጋር ቀድሞ ወደ ገነት እንዲገባ በሩ እንደ ተከፈተለት የሚያስረዳ ጥልቅ የነገረ ድኅነት ትምህርት ነው።

ከዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊና የቅዱሳን አበው አስተምህሮ በመነሣትም እኛ ለዕፀ መስቀሉ እጅግ ታላቅ ክብር እንሰጣለን፤ የጸጋ ስግደትም እንሰግዳለን። ይኸውም ስግደቱ ዕፁን (እንጨቱን) ማምለካችን ሳይሆን፤ በላዩ ላይ ተሰቅሎ ዓለምን ላዳነው ለጌታችን

ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጥ የፍቅር፥ የአክብሮትና የአምልኮት ስግደት ነው።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ “ሌላ ትምክሕት ከኔ ይራቅ እንዳለ” ሌላ መመኪያ የለንም። ዕፀ መስቀሉ የክርስቲያኖች የድል አርማ፥ የአጋንንት ማሳደጃና ታላቅ የድኅነት ትምክሕት ነው።

ቤዛችን፥ መድኃኒታችን፥ ኀይላችንና ጽናታችን መስቀል ነው፤

ሀ. ቤዛችን ነው፤

ከላይ የተመለከትነው የዕፀ መስቀሉ ምሥጢር እንዳለ ሆኖ፥ ከዚህ ባለፈም መስቀል ማለት በጣም ሰፊ ነገረ መለኮታዊ ትርጉም ያለው ነው። ይኸውም የክርስቶስ መስቀል ማለት የሰው ልጅ ከኀጢአትና ከዘለዓለም ሞት ነፃ የወጣበት፥ መለኮታዊ ፍቅርና ቤዛነት የተገለጠበት የድል አድራጊነት ምልክት ማለት ነው። በቋንቋችን “ቤዛ” ማለት ምትክ፥ ካሳ ወይም አንድን የተያዘን/የታሰረን ነገር ዋጋ ከፍሎ ነፃ ማውጣት (መዋጀት) ማለት ነው። ስለዚህ “መስቀል ቤዛነ” ስንል እኛ በኀጢአት ምክንያት ወድቀንበት ከነበርነው የባርነት ዐዘቅት ነፃ የወጣንበት፥ መለኮታዊ የካሳ ዋጋ የተከፈለበት ይህ መስቀል ታላቅ የነፃነታችን ምልክት ነው ማለታችን ነው (ኤፌ. 1÷7)። በመስቀል ላይ የተከፈለው ዋጋ በጥቂት ቁሳዊ ነገር በወርቅ ወይም በብር የተደረገ መዋጀት ሳይሆን፥ ፍጹምና ነውር በሌለው በክርስቶስ ክቡር ደም የተከፈለ ነው። (1ኛ ጴጥ. 1÷18፡19)

ለ. መድኃኒታችን ነው፤

በዮሐንስ ወንጌል ላይ እንደተመዘገበው ጌታችን እንዲህ ብሏል፦ “ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ፥ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል።” ይህ በመስቀሉ የተገኘው ቤዛነት ለሥጋችን ብቻ ሳይሆን የዘለዓለም ሞት ለተፈረደባት ነፍሳችንም እውነተኛ “ፈውስና መድኃኒት” ሆኖ ቀርቧል።

በምድረ በዳ የናሱን እባብ ያዩት ከሥጋዊ መርዝ እንደዳኑ ሁሉ፥ ዛሬም በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን በእምነት የሚያዩ ሁሉ ከነፍስ መርዝ (ከኀጢአትና ከገሃነም) ይድናሉ”። በመሆኑም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነፍሳችንን ከዘለዓለም ጥፋት ያዳነ መድኃኒታችን በመሆኑ፥ ሐዋርያው ብቸኛ ትምክሕቱ አድርጎ ያቀርበዋል።

መስቀል ኀይላችን ነው!

ሐ. ኀይላችን ነው፤

ነፍሳችን በመስቀሉ መድኃኒትነት ከዳነች በኋላ፥ ሁልጊዜም በምድራዊ ጉዟችን ላይ የሚገጥሙንን የሰይጣን ፈተናዎችና የኀጢአት ጦርነቶች የምናሸንፍበት “ኀይላችን” ነው። የኢየሩሳሌሙ አባት ቅዱስ ቄርሎስ በምሥጢረ ጥምቀት ትምህርቱ' (ትምህርት 13) ላይ፦ “በግንባርህና በነገሮች ሁሉ ላይ የመስቀልን ምልክት ለማድረግ አትፈር፤ እርሱ የአጋንንት ማባረሪያ፥ የቅዱሳን መታወቂያና የላቀ ኀይል ነውና” ይላል። ሐዋርያውም “አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ በእርሱ (በመስቀሉ) ድል ነሥቶአቸው በግልጥ አሳያቸው” በማለት እንደመሰከረው (ቈላስ. 2÷15)፥ መስቀል የአጋንንትን ኀይል የሰበረ መለኮታዊ የጦር መሣሪያ ነው። በመስቀል ምልክት ፈታችንንና መላ ሰውነታችንን በምናማትብበት ጊዜ አጋንንት እንደ ጢስ ተነው፥ እንደ ትቢያ በነው የሚጠፉትም ስለዚህ ነው። “ወከዊነ ዐቲብሰ በአጽባዕት በእንተ ሰዲደ አጋንንት ውእቱ -- በጣት የማማተብ ሁኔታም አጋንንትን ለማባረር ነው”፤ “በከመ ይቤ እግዚእነ ለእመ ኮንኩ አወፅእ አጋንንተ በአጽባዕተ እግዚአብሔር -- ጌታችን እኔ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆነ” ብሎ እንደተናገረ፤ (ፍት.ነገ.አን. 14÷532፤ ሉቃ. 11÷20)።

በመሆኑም እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ በመስቀሉ ምልክት በእምነት ጠላት ሰይጣንን ድል ስለሚያደርግ፥ መስቀል ዕለት ዕለት የምንመካበት የእግዚአብሔር ኀይል ነው።

መስቀሉን ልንሸከም ይገባናል፤

እኛ የመስቀሉን ቤዛነት፥ መድኃኒትነትና ኀይልነት የተቀበልን እኛ ሁላችን ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ልንመካበት ብቻ ሳይሆን በተግባር በሕይወታችን ሊገለጥና ልንሸከመውም ይገባል። በሉቃስ ወንጌል እንደተመዘገበው ጌታችን፦ “ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽልኣ ለነፍሱ፤ ወያጥብዕ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ፥ ወይትልወኒ፤ ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ፥ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ” (ማቴ. 16÷24) በማለት ያዘዘን ትእዛዝም ይህንን ያረጋግጣል። ሥጋዊ ፈቃድን መግታት፥ መከራን በትዕግሥት መቀበልና ዓለምን መካድ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ተግባር ነው።

መስቀሉን ተሸክመን የክርስቶስን ፈለግ ስንከተል፥ “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት” የሚለውን የቅድስና ማንነት እንለብሳለን። አዎን! የጌታን ስቅለት ያመነ አማኝ በቃሉ ብቻ ሳይሆን በሕይወቱ መስቀሉን ይሸከማል። ቅዱስ ጳውሎስ፦-

መስቀል ኀይላችን ነው!

ወእለሰ በክርስቶስ፤ የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ፥ ሰቀሉ ሥጋሆሙ ምስለ ፍትወት ወነጢአት፤ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ (ገላ. 5÷24) እንዳሉ፥ መስቀሉን መሸከም ማለት ክፉ ምኞትን/የኀጢአት ፍላጎትን፥ አሮጌውን ማንነትና የሥጋን ፈቃድ በኅሊናው የመስቀል/የመግደል መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው።

የመስቀሉ ጠላቶች፤

የመስቀሉ ምሥጢር፥ ጸጋና በረከት ለክርስቲያኖች የሕይወትና የድኅነት መንገድ ሲሆን፤ ለዚህ ዓለም ጥበበኞች፥ ለአይሁድና ለመናፍቃን ግን የመስቀሉ ኀይልና ምልክት የማይዋጥላቸው ዕንቅፋት ሆኖባቸዋል። የመስቀሉን ምልክት ያቃልላሉ፥ ክብር የሚገባው መሆኑንም ይክዳሉ። ነገር ግን ይህ ክሕደት አዲስ ሳይሆን ገና ከመጀመሪያው የነበረና በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠ ነው። "ንሕነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቅለ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው" (1ኛ ቆሮ. 1÷23) እንዳለ፤ አይሁድ የሚጠብቁት ምድራዊ ንጉሥና በኀይል የሚገዛ መሲሕን ስለነበር፥ በመስቀል ላይ የተሰቀለና መከራ የተቀበለ አምላክ ለእነርሱ የዕንቅፋትና የመሰናከያ ድንጋይ ሆኖባቸዋል። የአሕዛብ ፈላስፎችም ቢሆኑ እነርሱ ከሚመኩበት ሰዋዊ ዕውቀት አንጻርና በፍልስፍና ዐይን ሲመለከቱት፥ "አምላክ ፍጡሩን ለማዳን በመስቀል ላይ ሞተ" የሚለው ልዩ መለኮታዊ ጥበብ ለአእምሮአቸው እንደ እብደትና እንደ ሞኝነት ሆኖ ታይቷቸዋል።

ሐዋርያው ግን "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው..." (ፊልጵ. 3÷18፡19) በማለት የመስቀሉ ጠላት መሆን ወደ ዘለዓለም ጥፋት የሚያደርስ ክሕደትና ኀጢአት መሆኑን በዕንባ ጭምር ያስጠነቅቃል።

የምእመናን እምነትና ትምክሕት፤

መናፍቃንና የዚህ ዓለም ሰዎች ቢክዱትና ቢቃወሙትም፥ የመስቀሉ ኀይል ግን የሕይወታችን መዳን የተገኘበት የእግዚአብሔር ኀይል ነው። አማኞች የመስቀሉን ምልክት በእምነት በማማተብ የዲያብሎስን ፈተናና እኩያን መናፍስትን ያርቃሉ። እንዲሁም ከላይ እንደተገለጸው በላዩ ላይ የተከፈለውን ክቡርና ቅዱስ ዋጋ እያሰቡ መስቀሉን በሕይወት ይኖሩታል።

ስለዚህ ዓለም ቢክደውም፥ እኛ ግን ከሐዋርያው ጋር ሆነን "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" እያልን በመስቀሉ ይበልጥ እንታመናለን፤ ፈታኙንና መላ ሰውነታችንን እናማትብበታለን። በትእምርተ መስቀል በምናማትብ ጊዜም መድኀኒታችን ክርስቶስ ስለእኛ ሲል ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ የተቀበለውን መከራውን፥ ስቅለቱን፥ የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን፥ በጦር የተወጋ ጐኑን፥ በራሱ ላይ የተዳፋውን የእሾኽ አክሊል በአጠቃላይ ሕማሙን፥ ሞቱን፥ እያሰብንና እያሰላሰልን ነው የምናማትበው። በልባችን ውስጥም የድኅነታችን ምልክት (አርማ) አድርገን ለዘለዓለም እንይዘዋለን። ስለዚህ ዓለም ብትክደውም፥ አምነን የዳንበት እኛ ኦርቶዶክሳውያን ግን በመስቀሉ ኀይል ዘወትር እንመካለን።

መዐዛመዒ ያ፤

በእኛ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፥ ምእመናንና ካህናት ዘንድ በዘወትር ጸሎታችን ሁሉ ዕለት ዕለት እገዚአብሔርን በምናመሰግንበት ጊዜ በአንድ ድምፅ የምንናገረው ታላቅ የመስቀል ምስክርነት አለ፤ እሱም፦ "መስቀል ኀይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ መስቀል መድኀኒተ ነፍስነ፤ አይሁድ ክሕዱ ንሕነሰ አመነ ወእለ አመነ በኀይለ መስቀሉ ድኅነ፤ መስቀል ኀይላችን ነው፤ መስቀል መጽናኛችን ነው፤ መስቀል ቤዛችን (መዋጃችን) ነው፤ መስቀል የነፍሳችን መድኀኒት ነው። አይሁድ ካዱት፤ እኛ ግን አምነናል፤ ያመነውም በመስቀሉ ኀይል ድኅነትን አግኝተናል" የሚለው ቃል ነው። ይህም ተራ ምስክርነት ሳይሆን ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ የድኅነት አዋጅ ነው።

እኛ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ስንመላለስ እንደ ዓለም ሰዎች በሥጋዊ ሀብት፥ በምድራዊ ዕውቀት፥ በዘር፥ በሥልጣን ወይም በኀይል አንመካም፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ የሚያልፉና ጠፊዎች ናቸው። የእኛ እውነተኛና ዘላቂ ትምክህታችን የጌታችን የመድኀኒታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀሉ ነው። "ወአንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜነር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ወበኀቤየሰ ምዉት ዓለም፤ ወአነሂ ምዉት በኀበ ዓለም፤ ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፥ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ።"

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



"የጽኑ ተስፋችን መሠረት መስቀል ነው።"

(2ኛ ጴጥ. 1÷4፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

በመጋቤ ብርሃናት አባ ተክለ ያሬድ ኀርኀርዮስ (ቆሞስ)
የቅዱስ ሲኖዶስ ም/ዋና ጸሐፊ

መስቀል ኀይላችን ነው!

ተስፋ ማለት በዚህ ዓለም ብቻ የማይወሰን፥ ወደ ዘለዓለማዊ ክብር የሚመራ፥ በሙሉ መታመንና መከራን በመታገሥ በቅድስና እየኖርን መጪውንና የማይታየውን ርስተ መንግሥተ ሰማያት በእምነት የምንጠብቅበት፥ በመስቀሉና በትንሣኤው ድል የተመሠረተ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። (የሐዋ. ሥራ 13÷32፤ ሮሜ 8÷24፤ 9÷8፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት)

በጊዜው የሚፈጸመው፥ ጥልቅ በሆነ ሥነ-መለኮታዊና ታሪካዊ ትርጉም የተሞላው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ተስፋ፦ የትድግና ተስፋ፥ የተፈጸመውና የሚጠበቀው ተስፋ በሚሉ ሦስት አርእስት የሚከፈል ነው:: (ሮሜ 15÷13)

የትድግናው ተስፋ፤

ጠላት ከሚያደርሰው ክፉ ነገር ሰውን የሚጠብቀው የትድግናው ተስፋ በመከራ ጊዜ የሚታደግ፥ የሰው ልጅ በቅድስና እንዲኖር የሚያነሣሣ፥ በዚህ ክፉ ዓለም የሚያጋጥመውን ፈተና በትዕግሥት እንዲሸከም የሚያበረታታ፥ በመግባትና በመውጣት በሚኖረው ዕለታዊ የሰው ሕይወት ላይ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። (መዝ. 120÷8)

በመስቀሉ ኀይል ሁሉን የሚደግፈው የትድግናው ተስፋ፦ ሰውን ከሞተ ግብት (ከድንገተኛ ሞት) በመታደግ ዕለታዊ ችግርን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን በችግሩም ውስጥ ሆኖ እንዲጸና ሁሉን የሚያስችለውን ጸጋና ኀይል የሚሰጥም ጭምር ነው።(ዕብ. 1÷3)

በአጠቃላይ በሥጋዊ ሕይወታችን የምናገኘው ሲሳየ ዕለት፥ ጤናው፥ ሰላሙ፥የማይቋረጠው ጥበቃውና ሌሎችም በጎ ስጦታዎችና ፍጹምም የሆነው በረከት ሁሉ የእግዚአብሔር ትድግና መገለጫዎች ናቸው። (ያዕ. 1÷17)

የተቋደመው ተስፋ፤

የተስፋው አምላክ እግዚአብሔር በማይታበለው ቃሉ፥ በጽኑዕ ኪዳኑ ከዓለም ጥፋት እንድናመልጥበት አስቀድሞ ለአበው የሰጠው ተስፋ፦

- በዘለዓለም ቤዛነት፥በመስቀሉ ሥራ ከኃጢአት እስራትና ከዘለዓለም ፍርድ የአመኑትን ሁሉ ነጻ በማድረግ፥ (ዕብ. 9÷12)
- ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ፥ (ኤፌ 2÷3)
- በስሙ የተጠመቁት ሁሉ ሀብተ ውልድና፥ ሕይወተ ልቡና እንዲያገኙና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንዲሆኑ ከማድረግ ጋር፤ ‹‹እግዚአብሔር ያድናል›› የሚለውን የስሙን ትርጉም በትክክል በማረጋገጥ ተፈጽሞአል። (ሉቃ. 1÷21፤ ገላ. 4÷4-7)

በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነው እግዚአብሔር በመስቀሉ የፈጸመውን የማዳን ሥራ በሙታን መነሣት ቀን ዳግመኛ ሲመጣ ሕያዋን ሆነን፥ በደመና ተነጥቀን ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንድንኖር በፍጹም ክብር ስለሚያጠናቅቀው፥ የሚጠበቀው ተስፋ በእምነት ሲታሰብ ልብን ደስ የሚያሰኝ የሕይወት ስንቅ ነው። (1ኛ ተሰ. 4÷17)

የሚጠበቀው ተስፋ፤

- በአዘጋጀልን ስፍራ ከእርሱ ጋር ሊያኖረን እንደ ተስፋ ቃሉ በክብርና በኀይል የሚሆነው ዳግም ምጽአቱ፥ (ዮሐ.14÷3)
- ‹‹የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን ›› እያልን ዘወትር በእምነት የምንጠብቀው ትንሣኤ ሙታን፥ (1.ቆሮ 15÷42)
- በነቢያቱ አፍ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ የተነገረው፥ በትዕግሥት የምንጠብቀው፥ ለክብር ትንሣኤ ተነሥተን የምንወርሰው የሚመጣው ዘለዓለማዊ ሕይወት፥ (ሮሜ 1÷1)
- ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈው በክብር የምንኖርበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚጠበቀው ተስፋ ነው። (ራእ. 21÷1-4)

በመሆኑም የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ላይ የተገለጠበት መስቀሉ በሦስት ተከፍሎው ለቀረቡት የተስፋ ስጦታዎች ማእከል ነው። የተባረከው፥ የሚጠበቀውና የፍጻሜው ተስፋም ምእመኑን በሥጋዊ ሕይወቱ በቅድስና፥ በትዕግሥት፥ በፍቅርና በጽናት እንዲኖር የሚያደርግ በመስቀሉ የተገኘ መንፈሳዊ ኀይል ነው (ቲቶ 2÷13)። በአፈ ነቢያት ከተነገረው፥ በመስቀሉ ከሚፈጸመው ጽኑ ተስፋ አንጻር መዳኑን ሲጠባበቅ የነበረው ፍጥረተ ሰብእ የጽኑ ተስፋው መሠረት ከሆነው የክርስቶስ መስቀል በቀር ወደ ሕይወት ሀገር የሚያደርሰው ሌላ ተስፋ እንደሌለው፦ «መስቀል ውእቱ በትረ ተስፋነ በውስተ ዝንቱ ገዳም ዘያበጽሐነ ኀበ ሀገረ ሕይወት ቅድስት አልቦ ለነ ተስፋ ካልእ ዘእንበሌሁ ÷ በዚህ በረሀ (ምድራዊ ሕይወት) ውስጥ የተስፋ ምርኩዛችን መስቀል ነው፤ ወደ ቅድስት የሕይወት ሀገር (መንግሥተ ሰማያት) የሚያደርሰን፤ ከእርሱ በቀር ሌላ ተስፋ የለንም»

የጽኑ ተስፋችን መሠረት መስቀል ነው።

መስቀል ኀይላችን ነው!

በማለት ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሰውን ልጅ ምድራዊ ሕይወት በበረሀ ጉዞ በመመሰል ነገረ መስቀሉን በፍቅር ዕንባ ከልዩ ተመስጦ ጋር ሰብኮታል።

ሊቀ ካህናት ክርስቶስ እኛን ከጻድቃን ጋር ሊደምረን ከጊዮን ጋር ተቆጥሮ በፈጸመው የማዳን ሥራም መስቀሉ ለሰው ልጅ የልብ መብራት፥ የነፍስ መጽናኛ፥ የእምነት መሠረት ስለሆነ ልብን በእምነት ያጸናል፤ በመከራ ጊዜ ያቆማል፤ ከአስቸጋሪው ዓለም ለይቶ ወደ እርሱ በተስፋ ያደርሳል። (ኢሳ. 53÷21)

በመሆኑም ተኰለቁ ምስለ ጊዮንን ከመ ይደምረነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን ÷ ከጻድቃን ነፍሳት ጋር አንድ ያደርገን ዘንድ ከበደለኞችጋር ተቈጠረ» እንዳለው ሊቁ፥ ከወንበዴዎች ጋር በመስቀል ተሰቅሎ ከጻድቃን ነፍሳት ጋር የተቈጠርንበት፥ ወደ ሀገረ ሕይወት የገባንበት የመስቀሉ ጽኑ ተስፋ ወደ እውነተኛው ወደብ (ወደ ክርስቶስ) የተሻገርንበት የድኅነታችን ምሥጢር፥ የትንሣኤ፥ የይቅርታና የዘለዓለም ሕይወት ፍጻሜ መሆኑ አያጠራጥርም።

ለክብር የበቃንበት የድኅነታችን ፍጻሜና የጽኑ ተስፋችን መሠረትም "እነሆ እግዚአብሔር መድኃኒቴ ነው፤ በእርሱ እታመናለሁ፤ አልፈራም" የሚለው፥ አስቀድሞ የተነገረው ቃለ ነቢይ ነው። (ኢሳ. 12፥2)

መስቀል ወደ ወደቡ የሚያሻግር የተስፋው መርከብ ነው፤

ነፍሳችንን ወደ ሰማያዊ ተስፋ የሚያደርሰው፥ የሥልጣናትና የኀይላት ሁሉ ራስ የሆነው ሐዳፌ ነፍስ ክርስቶስ፥ በቀራንዮ የተሰቀለበት መስቀል በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ ከመከራ ማምለጫ፥ የአመኑትን ሁሉ በሰላም ወደ አስተማማኙ ወደብ የሚያሻግር፥ የማይጠፋና የማያረጅ የተስፋ መርከብ ነው (ቈላስ. 2÷10)። ይህም እውነታ «መስቀል ውእቱ ሐመር ዘይሔድፍ ዲበ ማዕበለ ዝንቱ ዓለም፤ ወያበጽሕ ነፍሳተነ ኀበ ተስፋ ሰማያዊት ÷ በዚህ ዓለም ማዕበል ላይ የሚቀዝፍ (የሚጓዝ) መርከብ መስቀል ነው፤ ነፍሳችንንም ወደ ሰማያዊ ተስፋ ያደርሳል» ተብሎ ተገልጦአል። (ውዳሴ መስቀል)

ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ጥልቅ በሆነው ትምህርቱ፥ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ አጥንትን በሚያለመልመው የዜማ ድርሰቱ፥ በመስቀል ሞት መሸነፉንና ለፍጥረት ሁሉ እውነተኛው የሕይወት መንገድ መታደሱን፥ የመጀመሪያው ተስፋ በድኅነተ ሰብእ መፈጸሙንና የመጨረሻው ተስፋ መንግሥተ ሰማያትም የሚፈጸም መሆኑን፥ «መስቀል ውእቱ ተስፋሆሙ ለኃጥኣን እለ ይኔስሑ፤ ወዐቀብተ ጽድቆሙ ለጻድቃን መስቀል ውእቱ ኮከበ ተስፋ ዘነግህ፤ዘያሰስል ጽልመተ ወያበርህ አእምሮ ኵልነ ሕዝብ ንሰብክ ኀይሎ ወስብሐቶ ÷ ጨለማን አሳድዶ አእምሮን የሚያበራ የእውነተኛ ተስፋ የንጋቱ (የማለዳው) ኮከብ መስቀል ነው፤ እኛ ሕዝቡ ሁላችንም ኀይሉንና ክብሩን እንሰብክለን ÷ መስቀል ንስሓ ለሚገቡ ኃጥኣን ተስፋቸው ነው፤ ለጻድቃንም የጽድቃቸው ጠባቂ ነው›› በማለት ልብን በሚነካ ድንቅ ምሥጢር ተባበረው አመስጥረውታል።

በጎምዘ ከይሲ (በእባቡ መርገዝ) የቈሰሉትን ሁሉ በመገረፉ ቍስል ይፈውሳቸው ዘንድ በተሰቀለበት መስቀሉ ላይ የተገለጠውን መለኮታዊ ፍቅርም፦ «ነአምኖ ለመስቀል ቅዱስ፤ እስመ ውእቱ ተስፋ ለቅዱሳን፥ ወመርሶ ለአሕማር አክሊሎሙ ለሰማዕት፤ ወሎቱ ንሰግድ ኵልነ እለ አመነ በክርስቶስ ÷ ቅዱስ መስቀልን እናምነዋለን፤ እርሱ ለቅዱሳን ተስፋቸው፥ የመርከቦች ወደብ፥ ለሰማዕታትም አክሊላቸው ነውና በክርስቶስ ያመንን ሁላችንም ለእርሱ እንሰግድለታለን።»

«መስቀል ውእቱ ልብሰ ተስፋሆሙ ለዕሩቃን፤ ወማኅፈዲ ድኅነቶሙ ለኃጥኣን በጎይለ መስቀሉ ለክርስቶስ ተነድገ ለነ አበሳነ ÷ መስቀል ለታረዙት (ክብራቸውን ላጡት) የተስፋ ልብሳቸው ነው፤ ለኃጥኣንም የመዳኛ መጠለያቸው ነው። በክርስቶስ መስቀል በደላችን ተወገደልን» በማለት መስቀል የእውነተኛው ተስፋ ፍጻሜና የክብር ልብስ መሆኑን ሊቁ በማይታበለው ምስክርነቱ መስክሮልናል። (ቅዱስ ያሬድ)

መስቀል ሰማያዊ ተስፋ ያገኘንበት÷ በገነት መካከል ያለው የሕይወት ዛፍ ነው፤

በኦሪት ዘፍጥረት የተጠቀሰው፥ ጥበብን፥ ተስፋንና በሕይወት መኖርን የሚወክለው «ዕፀ ሕይወት ÷ የሕይወት ዛፍ» በሐዲስ ኪዳን የመስቀል ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል። (ምሳ. 3÷18)

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የመስቀልን ዘለዓለማዊ ሕይወትነትና ተስፋነቱን ሲገልጥ፥ «መስቀል ውእቱ ዕፀ ሕይወት ዘማእከለ ገነት፤ ዘቦቱ ረከብነ ተስፋ ሰማያዊተ ÷ በገነት መካከል ያለው የሕይወት ዛፍ መስቀል ነው፤ በእርሱም ሰማያዊቱን ተስፋ አገኘን» ብሎአል። በመስቀሉ ሰማያዊ ተስፋ በማግኘታችንም «አንተ ውእቱ ዕፀ ሕይወት ዘነበረ በማእከለ ገነት ÷ በገነት መካከል የነበረ የሕይወት ዛፍ አንተ ነህ» እያለ ለክብሩ የሚሆነውን ውዳሴ ያለመሰልቸት ያቀርባል።

የጽኑ ተስፋችን መሠረት መስቀል ነው።

መስቀል ኀይላችን ነው!

የዓለሙን ኀጢአት የሚያስወግደው የፋሲካው በግ ክርስቶስ የተሠዋበትን መስቀል ማኅሌታይ ያሬድ «መድኀኒት ዕፀ ሕይወት ዝንቱ ውእቱ መስቀል ÷ መድኀኒት የሕይወት ዛፍ መስቀል ነው» በማለት የመስቀልን መድኀኒትነት በአማረ የዜማ ስልት፥ በዐውደ ትርጓሜ ሰገነት ከፍ አድርጎ በክብር ያውጃል። ይህም ቃል የሚያሳየው መስቀል በክርስቲያኖች ዘንድ የሚታየው እንደ ተራ ዕፅ ሳይሆን፥ የሞት ኀይል የተሸነፈበት፥ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀበትና የዘለዓለም ሕይወት የተገኘበት መሆኑን ነው።

መስቀል ሰማይና ምድርን፥ እግዚአብሔርንና ሰውን ያስታረቀ የፍቅር ድልድይ በመሆኑ ተዘግቶ የኖረው ገነት ተከፍቶ የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለሱ ዋነኛ ተስፋ ነው። ሰማያዊ ተስፋ የአገኘንበት፥ በገነት መካከል ባለው አዲሱ የሕይወት ዛፍ መስቀል ላይ የተፈጸመው ምሥጢረ አድኅኖ፦

- ሞትን ወደ ሕይወት፥ እርግማንን ወደ በረከት ለውጦአል።
- የሞት መሳሪያ የነበረውን መስቀል የሕይወት መንገድ፥ የሽንፈት ምልክት የነበረውን የድል ምልክት አድርጎአል።
- የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆአል።
- የዘለዓለም ሕይወት ተስፋን አረጋግጦአል።

በአጠቃላይ መስቀል ለክርስቲያኖች የተስፋ ሁሉ ምንጭ ሆኗል። መዳናችን የተረጋገጠበት መስቀል በአበው አስተምህሮ «የሕይወት ዛፍ» ተብሎ የሚተረጐመው በእርሱ በኩል ለሰው ልጅ የዘለዓለም ሕይወት ተሰጥቶ የገነት በር ስለተከፈተ ነው።

መስቀል የክርስቲያን ተስፋ÷የድኀነት አርማ ነው፤

ከኀጢአት ፥ከሞትና ከሰይጣን ባርነት ነጻ የወጣንበት የድኀነታችን አርማ የሰማያውያንና የምድራውያን መገናኛ በሆነው መስቀሉ የተገለጠው ፍቅር ለብዙ ዓመታት ሲጠበቅ የቆየው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (ዮሐንስ ዘደማስቆ)። ይህንም ጸጋ ለመቀበል በማያሳፍረው ተስፋ ጸንቶ ለመኖር የተስፋው ሰው፥ የብዙ አሕዛብ አባት የሆነው አብርሃም ታላቅ ምሳሌ ነው። እስከ ሞት ድረስ የሚታዘዝለት ልጅ እንደሚወለድለት እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ለብዙ ዓመታት በትዕግሥት ጠብቆ በእምነት ጸንቶ ኖረ፤ ሆነለትም (ሮሜ 4÷18-21)። ምሳሌ በሚሆነው በዚህ ፍኖተ ጽድቅ እየተጓዘ የክርስቶስ መስቀል የድል፥ የፍቅር፥ የሕይወትና የተስፋ ምልክት የሆነለት ሰው ልቡ እግዚአብሔርን በማመን የተተከለ ገነት ነው።

ሁኔታዎች ቢለዋወጡም ድኅነቱ በመስቀሉ በኩል በተሰጠው የእግዚአብሔር ጸጋና በእርሱ መታዘዝ የሚቀጥል የሕይወት ጉዞ መሆኑን ከነገረ መስቀሉ ስለሚረዳ ተስፋው አይናወጥም፤ ልቡም አይታወክም (ኤፌ.1÷18)። በአሁኑ ክፉ ዓለም በተኩላዎች መካከል እየተመላለሰ በኀይለ መስቀሉ በእምነትና ግብዝነት በሌለበት ፍቅር ጸንቶ ይኖራል፥ በጸሎት ይበረታል፥ የዘለዓለም ሕይወትንም በተስፋ ይጠባበቃል። ንጉሥ ለወደደው እንዲህ ይደረግለታልና «ወቦቱ ይሣሀሎ ለኵሉ ÷ ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለዋል። (ቈላስ. 1÷20)

በመሆኑም የክርስቲያን ተስፋ፥ የመዳኑ አርማ ዋና መሠረቱ የክርስቶስ መስቀል ነው። መስቀሉ መከራን ወደ ድል፥ ሞትን ወደ ሕይወት፥ ጥፋትን ወደ ድኅነት ይለውጣልና፥ ክርስቶስ ዘወትር በእኛ ልብ ውስጥ ያለ የክብር ተስፋ ነው (ቈላስ. 1÷27)። እንደ ተስፋ ቃሉ በተፈጸመው ድኅነትም መስቀሉ የመርገም ምልክት መሆኑ ቀርቶ ትእምርተ ድኅነት ሆኖአልና፥ በክርስቶስ ቤዛነት፥ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት የተዋጁት ሁሉ (ክርስቲያኖች) በእምነት ለሚወርሱት መንግሥተ ሰማያት ጽኑ መሠረት እርሱ ነው።

የክብር ትንሣኤንና የዘለዓለም ሕይወትን ያበሠረው የድኅነታችን አርማ መስቀል የኀጢአት መደምሰሻ፥ የሕይወት መገኛ፥ ሞት በሕይወት የተዋጠበት ጽኑ ተስፋ ስለመሆኑም፦ «መስቀል ውእቱ መንሥኢሆሙ ለምውታን፥ ወመድኀኒቶሙ ለሕያዋን፥ ወመዊአ ፀር ኀይል ውእቱ ልዕልናሃ ለቤተ ክርስቲያን፥ ወተስፋ ኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ÷ መስቀል የሙታን ትንሣኤቸው፥ የሕያዋንም መድኀኒታቸው፥ጠላትን ድል የሚያደርግ ኀይል፥ የቤተ ክርስቲያን ከፍታዋ (ልዕልናዋ)፥ የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ተስፋና የምስጋናቸው ምንጭ ነው›› ተብሎ ተጽፎአል።

ቅዱሱ አባ ጊዮርጊስም «ሰላም ለከ ኦ መስቀል፥ ዘሀሎከ ቀዳሚ ኀበ ነቢያት በምሥጢር፤ ወኀበ ሐዋርያት በክብር አንተ ውእቱ በትረ ሙሴ ዘፈለገ ባሕር ÷ በነቢያት ዘንድ አስቀድሞ በምስጢር፥ በሐዋርያትም ዘንድ በክብር የነበርክ መስቀል ሆይ፥ ሰላምታ ይገባሃል። ባሕሩን የሰነጠቀው የሙሴ በትር አንተ ነህ፤ በገነትም መካከል የነበረው የሕይወት ዛፍ አንተ ነህ» እያለ መስቀል የነቢያት ትንቢት ፍጻሜና የሕይወት ምንጭ መሆኑን ይነግረናል። በአሕዛብ ልማድ የሞትና የውርደት ምልክት የነበረውን ቅዱስ መስቀልም ፍኖተ ሕይወት

መስቀል ኀይላችን ነው!

ክርስቶስ ወደ ዘለዓለም መንግሥት መሸጋገሪያ ድልድይ ስላደረገው ኢትዮጵያዊው ጻድቅ፥ የሰግላው ሊቅ፦ «የመንገድ ተስፋ» ብሎ ይጠራዋል።

እውነተኛው ክርስቲያን ከጨለማው ሥልጣን የዳነበት የድኅነቱ ዙፋን፥ የመዳኑ አርማ የሆነውን መስቀል በዐይነ ኅሊናው ሲመለከት የሚረዳው የተገኘውን የድል የሕይወትና የገነት በር መከፈቱን እንጂ መስቀል የመከራ ምልክት ብቻ መሆኑን አይደለም (ቈላስ. 1÷13-19)። በመሆኑም የመከረኛው ዓለም እውነተኛ ተስፋ ሀብት፥ሥልጣን ወይም የሰው ጥበብ ስላልሆነ በዚህኛው ዓለም ሲኖር መከራ ቢበዛበትም የክርስቲያን ተስፋ የሚወለደው በመስቀል ነው። በእርሱም የተገኘውን ድኅነት እያሰበ ያሸነፈበትን ምልክት በፊቱ ይዞ እምነቱንና ክርስቲያናዊ ጽናቱን አይተውም።

የድኅነቱ ሽልማት በሆነው መስቀሉ ተስፋ ያለው ሰው በመከራ ውስጥም ቢሆን ተስፋውን የማይተው፥ የወደፊቱን መልካም ነገር በእምነት የሚጠባበቅ ይሆናል።(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም)

በመስቀሉ ኀይል ጽኑ ተስፋ ያለው ክርስቲያንም፦

- በእግዚአብሔር ቃል ይታመናል።
- በመከራ ውስጥ ጽናትን ያሳያል።
- በጸሎት ይጸናል።
- በደስታና በሰላም ይኖራል።
- ሌሎችንም «በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤» (ሮሜ 12÷12)

«ተስፋን የሰጠው የታመነ ስለሆነ የተስፋችንን ምስክርነት ሳንናወጥ እንያዝ» (ዕብ. 10፥23)። «በእግዚአብሔር ተስፋ አድርግ» (መዝ. 42፥11)። "ተስፋ አያሳፍርም፤ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ፈሷል" እያለ በመስቀሉ በተገኘው የተስፋ ቃል ጸንተው እንዲኖሩ ያደርጋል። (ሮሜ 5÷5)

- «ወለነሰ ሀለወነ ክቡር መስቀል ዘአሥረጸ ወአፍረየ ለነ ፍሬ ሕይወት ÷ ለእኛስ የሕይወት ፍሬን ያፈራ ክቡር መስቀል አለን» በማለት ራሱን በእምነት ያኖራል፤ የሚታየውን ሳይሆን የማይታየውን በተስፋ ይጠብቃል። (2ኛ ቆሮ. 5÷7)
- በመከራ አይሸነፍም፤ መከራን እንደ ፈተና እንጂ እንደ ሕይወት መጨረሻ አይመለከትም። (ሮሜ 5÷3-5)

በመሆኑም መስቀል ያለፈ የመዳናችን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለሚመጣው ዘለዓለማዊ ተስፋ ነው ስንልም፥ በዋናነት ከክርስቶስ የማዳን ሥራ፥ ከትንሣኤው፥ከዘለዓለማዊ ሕይወትና ከእግዚአብሔር ፍቅር አንጻር ነው።

መስቀል በረከት የሚወርድበት የዕርቅ መሰላል ነው፤

እስመ ተዋለጠ እግዚአብሔር ዓለመ በክርስቶስ አናኅስዮ ኀጢአቶሙ ÷ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን አስታርቆአልና በደላቸውን አይቆጥርም። (2ኛ. ቆሮ. 5÷19) ዕርቅ የተፈጸመበት የክርስቶስ መስቀል ሁሉ እንዳይገናኙ በአዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛት ሕግን ሸሮ፥ በመካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሶ ሕዝቡንና አሕዛቡን አንድ ያደረገ፥ ሰማይና ምድርን ያገናኘ፥ በረከተ ሥጋን፥ በረከተ ነፍስን ያስገኘ እውነተኛ የዕርቅ መሰላል ነው። (ዮሐ 1÷51፤ ኤፌ 2÷14)

ጽድቁን በመስቀሉ ያሳይ ዘንድ የተደረገውን ኀጢአት ትቶ በእርሱ አማካኝነት በተፈጸመው ድኅነት የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት እርሱን ለማያመሰግኑት ሁሉ ለበጎውና ለክፉ አድራጊው በእኩልነት ተስጥቶአል (ሉቃ. 6÷35፤ ሮሜ 3÷25)። የበረከትና የዕርቅ መሰላል የሆነውን መስቀል ቅዱሳን አባቶች ከዐሥራው መጻሕፍት ተነሥተው በትርጓሜ ሐተታቸው፥ በምሥጢር ገበታቸው «መስቀል በረከት የሚወርድበት የዕርቅ መሰላል ነው» ብለው ይተረጕሙታል። ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ፥ ከገነት ተድላ ወጥቶ ለሞት በተሰጠ ማንነት የአምላኩን ፍቅርና በረከት አጥቶ የኖረው የሰው ልጅ ትልቁ ችግር የሥጋ ድኅነት፥ ሕመም ወይም ሞት ብቻ አይደለም ከእግዚአብሔር የለየው፥ ከበረከት ያጎደለው። በተቃራኒ ቦታ እንዲገኝ ያደረገው ኀጢአት ነው።

በመሆኑም ዕርቅ፥ ድኅነተ ነፍስን፥ በረከተ ሥጋን ለዓለም ሁሉ የሚያሰጥ ጽኑ ተስፋ የተገኘበት ዕፀ ሥርየት መስቀሉ የሰው ልጅ መዳንና በረከት፥ የአዲስ ሕይወት መክፈቻ፥ ወደ ትንሣኤ የሚወስድ መንገድና የዕርቅ መሰላል ነው።

መስቀል ፍርሀተ ሞትን ያስወገደ፥ የሚያልቅ ደስታን ያሰጠን፥ የአዲስ ፍጥረት መገኛ ነው፤

‹ወቀነዮ ሰይጣን በስሕተቱ ለአዳም ÷ በስሕተቱ ምክንያት ሰይጣን አዳምን ገዛው›› ተብሎ እንደተጻፈው፥ በኀጢአት ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ሞት በቀዳማዊ ልደት ገሸር ተብሎ በክብር ሲኖር ከነበረው አዳም እስከ ሙሴ፥ ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ድረስ ኀጢአት

የጽኑ ተስፋችን መሠረት መስቀል ነው።

መስቀል ኀይላችን ነው!

ያልሠሩትንም ጭምር ሳይለይ ሁሉንም ገዝቶ ኖሯል (ሮሜ 5÷14፤ ተረፈ ቁርሎስ)።ከሞት አገዛዝ የእኛን ነፃ መውጣትና ደስታ ማግኘት የሚሻው መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ በሞት ፍርሀት ዕድሜያቸውን ሁሉ በባርነት ተይዘው የኖሩትን ነፃ ያደርግ ዘንድ፦ ‹‹ወመነና ለነፍረተ መስቀል በእንተ ፍስሓሁ ዘጸነሐ ሎቱ ÷ተጠብቆለት ስላለ ደስታ የመስቀል ውርደትን ናቃት››። (ዕብ. 12÷2)

በመስቀሉም ሥልጣነ ሞትን ሽሮ፥ እኛ ሞትን የማንፈራ ይልቁንም ‹‹አይቴ እንከ ቀኖትከ ሞት ÷ ሞት ሆይ፥ መዊጊያህ የት አለ?›› እያልን በመስቀሉ የምንመካ አድርጎ የማያልቅ ደስታን ሰጠን፤ በወርቀ ደሙ ከሞት ግዛት ዋጀን። (ዮሐ 15÷11፤ 1ኛ ቆሮ. 15÷55)

ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳችን እንዳንኖር በደላችንን ሳይቈጥር አንዱ ስለሁሉ ሞቶ፥ አሮጌው ነገር አልፎ በእርሱ አዲስ ፍጥረት ሆነናል (2ኛ ቆሮ. 5÷17) አዲስ ፍጥረት ማለትም ውጫዊ ለውጥ ሳይሆን የልብ፥ የሐሳብ፥ የሕይወት ለውጥ ነው። በመሆኑም ሰው በመስቀሉ የተሰጠውን የድኀነት ስጦታ ሲያምንና ሲኖርበት ከፍርሀተ ሞት በትክክል ነፃ ይሆናል።

የሰው አዲሱ ማንነት የሚመጣው ሕይወትና ዘለዓለማዊ ክብር ዋስትናው መሆኑን በመስቀሉ የተገኘው ጸጋ በኀሊናው በኩል ይመሰክርለታልና፥ አዲሱን ሰው የለበሰው ተስፋው በመስቀል ላይ በተፈጸመው የማዳን ሥራ ላይ ይመሠረታል። በመሆኑም ፍርሀተ ሞትን ያስወገደው፥ የአሮጌው ሰው መሞቻ፥ የአዲሱ ሰው መወለጃ በሆነው መስቀል የተፈጸመው የማዳን ሥራ በመጨረሻው ቀን መንግሥተ ሰማያትን በማውረስ ከአሁኑ የበለጠ ይገለጣል። (ሮሜ 6÷6)

‹‹ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው›› የሚለው ታላቁ ምሥጢር፥ ወደ እግዚአብሔር የቀረብንበት ነገረ መስቀሉና የተሰፋው ፍጻሜ በጥልቀት ሲታይ፦

- ቅዱስ መስቀል የክርስቲያኖች መመኪያ፥
- የፍርሀተ ሞት ማስወገጃ፥
- የአጋንንት ማሸነፊያ፥
- የሞት መደምሰሻ፥
- የሕይወት በር መክፈቻና የሚያምኑት ሁሉ ሞትን የማይፈሩበት፥
- ይልቁንም የዲያብሎስን ሽንገላ የሚቃወሙበት ሥጋዊ ያልሆነ ንዋየ ሐቅል (የጦር ዕቃ) መሆኑ የማያጠራጥር እውነት ነው። (2ኛ ቆሮ. 10÷4)

በአጠቃላይ ዕፀ ሕይወት መስቀል የጽኑ ተስፋችን መሠረት የተባለው፦

- የነጢአት ይቅርታን በማስገኘቱ፥
- ሞትን በትንሣኤ በማሸነፉ፥
- ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቁ፥
- ለምእመናን የዘላለም ሕይወት ተስፋ በማሰጠቱ፥ በመከራ ውስጥ ጽናትንና ድልን በማጎናጸፉ፥
- የዕርቅና የዘላለም የሕይወት ተስፋ ምንጭ፥ መመኪያችንና ተስፋችን፥ የነፍሳችንና የሥጋችን መድኀኒት በመሆኑ ነው።

ሥልጣነ ሞት የተሻረበት፥ የማይቈጠር ጸጋ የተሰጠበት በመስቀሉ ላይ የተገለጠው ጽኑ ተስፋ በፍጹምነት የሚጠቀለለው በክርስቶስ ፍቅርና ትንሣኤ ላይ ተመሥርቶ በሚጠበቀው የዘላለም ሕይወት ተስፋ ነው። በመስቀሉ ፍጻሜውን ያገኘው ይህም ተስፋ ‹‹በዘቦቱ ነሐዩ ወነዐቢ ወንከብር›› ክሞት የዳንበት፥ ከጥፋት አምልጠን ከፍ ያልንበት የተከበረና እጅግም ታላቅ የሆነ ተስፋ ነው። (2ኛ ጴጥ. 1÷4)

በመሆኑም በመስቀሉ የተሰፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና ተስፋችን እንዳይጠፋ በእምነት እንጠብቅ። (ዕብ 10÷23)

ስለዚህም ቅዱስ መስቀል «በጎመ፡ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት ዕትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድጎክ ውስተ መርሕብከ ወእትቤ ትቤዘወከ በመስቀልየ ...» ተብሎ ለአዳም የተነገረው ተስፋችን የተፈጸመበት እንደመሆኑ፤ «ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል ወበቀራንዮ ተተክለ መድኀኒት መስቀል -- የአበው ተስፋ በማርያም ተፈጸመ፤ በቀራንዮም መስቀል ተተከለ» እያልን እንዘምራለን፤ በዓለ መስቀሉንም እናከብራለን።

"በኀይለ መስቀሉ ይዕቀበነ፤ ወይክሥት ኣዕይንተ ኣልባቢነ።"



“ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ
ለዘበምድር ወለዘበሰማያት ፡
በምድርም በሰማያት ላሉ በመስቀሉ
ደም ሰላምን አደረገ።።”

(ቈላስ. ፩፡20)

በመጋቤ ሐዲስ ጸጋ ወ/ትንሣኤ
የአብነቱ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ኀላፊ

ሰላም ለሰው ልጆች እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነገር ነው። አዳም ከእግዚአብሔር በተለየና ሕጉን ባፈረሰ ጊዜ እንዲፈራና እንዲሸሽ ያደረገው የውስጥ ሰላም ማጣት ነበር። በኀጢአት ምክንያት አሳዳጅ ሳይኖረው የሚሰደድ፣ ፈርቶም የሚደበቅ ድንጉጥና የኅሊና ዕረፍት የሌለው ሰው ሆነ።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነበት ዋነኛው ምክንያት አዳም በኀጢአት ምክንያት ያጣውን ሰላም ለመመለስ ነው። ይህንንም ለማስረዳት ጌታችን በተወለደበት ሌሊት በቤተ ልሔም የተገለጡ ቅዱሳን መላእክት “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ለዕንለ እመሕያው ሥምረቱ ÷ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድርም ለሰው በጎ ፈቃድ” በማለት ዘምረዋል። (ሉቃ. 2÷14)

ሰውና እግዚአብሔር፥ ሰማይና ምድር፥ ነፍስና ሥጋ፥ ሰማያውያን መላእክትና ምድራውያን የአዳም ልጆች ተለያይተው፣ በመካከላቸውም በኀጢአት ምክንያት የተገነባ የጥል ግድግዳ ስለነበረ፤ ያንን ግድግዳ አፍርሶ፥ ሰላማችንን መልሶ ሰማይንና ምድርን ስላስታረቀ፥ ለእግዚአብሔር ምስጋና በሰማያት ይሁን፤ በምድርም በሰው በጎ ፈቃድ ብለው ዘምረዋል። ይህ በምድርና በሰማያት የሆነው ሰላም የተፈጸመው በመስቀል ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም ነውና፤ ሐዋርያው “ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበምድር ወለዘበሰማያት ÷በመስቀሉ በፈሰሰው ደም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምን አደረገ” ብሏል።

በዓለም ታሪክ የደም መፍሰስ ሰላምን ሲያደፈርስ እንጂ ሰላምን ሲያመጣ የታየበት ዘመን የለም። የክርስቶስ ደም ግን ሰላምን እንዳደረገ ሐዋርያው ነገረን። በዓለም ላይ በየዘመኑ የሚፈስ የብዙ ንጹሓን ክርስቲያኖችም ደም ሚኞቹ የሚጎዱበት ባይሆንም የተፈጸመባቸው ግፍ ግን እግዚአብሔር የሚወደው፥ ለዓለምም ሰላምን የሚያመጣ አይደለም። የክርስቶስ ደም ግን ለሰው ልጆች ቤዛ ለመሆን በፍቅርና በፈቃድ ለቤዛነት የፈሰሰ ደም ነውና ለዘመናት ያጣነውን ሰላም የሚመልስ፥ ሰማይንና ምድርን የሚያስታርቅ ሆነ። ስለሆነም መስቀሉ

፫. የሰላም ምልክት ነው፤

መስቀሉ የሰላም ምልክት የሆነው በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም ሰላማችን ስለ ታወጀ ከሰላማችን ከክርስቶስ የተነሣ ነው። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን “ትእምርተ ሰላምነ ዘከያሁ ንትአመን ÷ በእርሱ የምንታመንበት የሰላማችን ምልክት” ይለዋል። ቅዱስ ያሬድም፦ “ወገብረ ሰላመ በጎይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ÷ በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኀይል ሰላምን አደረገ” ብሏል (ድጓ ዘመስቀል)። ስለሆነም መስቀል በክርስቲያኖች ዘንድ ጠላት ዲያብሎስ የታሰረበት፥ የጥል ግድግዳ ፈርሶ ሰላም የታወጀበት የሰላም ምልክት ነው።

ይህ በክርስቶስ መስቀል ያገኘነውና የምናገኘው ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ሰላም ግን አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን ሐዋርያትን፦ “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን

መስቀል ኀይላችን ነው!



አሸንፌዋለሁና” በማለት ስለሚጠቁቃቸው መከራ መስቀል ቢነግራቸውም፤ “ሰላሜን እተውላችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ሰላም አይደለም” ብሎ በመከራ መስቀሉ ውስጥ ስላለው ሰላም ነግሯቸዋል።

ስለዚህ ቅዱስ መስቀሉ ጥንትም ሰላም የታወጀበት፥ ዛሬም እየታሰርን እየሞትን ሰላም የምናገኝበት የሰላም ምልክት ነው። ክርስቲያኖች ትናንትም ዛሬም የገጠማቸውና የሚገጥማቸው መከራ በደስታ የሚቀበሉት በመከራ መስቀሉ ፍጹም ሰላምና የዘለዓለም ዕረፍት ስለሚያገኙ ነው። «እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ» (የሐዋ.ሥራ 5÷41) በማለት ቅዱስ ሉቃስ ገድለ ሐዋርያትን እንዳስተማረ፤ ነገር ግን “...የታረዱ ሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ፤ በታላቅ ድምፅ እየጮኹ፥ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም፤ ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም አሉ” ተብሎ እንደተጻፈ፥ የሰማዕታት ነፍስ ስለምትጠይቅ እግዚአብሔር ይፈርዳልና፤ አሳዳጆች ከመግደልና ከማሳደድ እንዲመለሱ፥ የሰላምን መንገድ እንዲከተሉ በክርስቶስ ፍቅር እንመክራለን (ራእ. 6÷9፡10)። እኛ ክርስቲያኖች ግን የሰላም ምልክት የሆነውን መስቀል ይዘን ሰላማዊ አለመሆን አንችልምና ከማሳደድ ይልቅ መሰሰድን፥ ከመግደልም ይልቅ መሞትን እንመርጣለን። (ማቴ. 5÷10-12)

2ኛ. ዕርቅ ምልክት ነው፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ወአብጽሖሙ ለክልኤሆሙ በአሐዱ ሥጋሁ ለነበ እግዚአብሔር ወበመስቀሉ ለጽልእ ቀተሎ ቦቱ ÷ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ያስታርቅ ዘንድ ነው” ይላል (ኤፌ. 2÷16)፤ ይህም መስቀሉ ጠላትነት የተወገደበት፥ ዕርቅ የተመሠረተበት፥ በደሙ የተቀደሰ የእውነተኛ ሰላም፣ የፍቅርና የእርቅ ምልክት እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ስለሆነም ክርስቲያኖች መስቀሉን ሲመለከቱ በመስቀሉ የተደረገውን ዕርቅ ይመለከታሉና፥ መስቀሉን ምልክት ያደረጉ ክርስቲያኖች መቼም ቢሆን በምንም ዓይነት ሁኔታ ለዕርቅ የሚዘጋ በር ሊኖራቸው አይገባም።

ሐዋርያው አሁንም “ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሣሀለነ በሞተ ወልዱ ÷ ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋራ በልጁ ሞት ታረቅን” በማለት መስቀሉ የዕርቅ ምልክት እንደሆነ ይነግረናል (ሮሜ 5÷10)። ጠላቶቹ ሆነን ሳለ ክርስቶስ በመስቀሉ ከእግዚአብሔር ጋር ከራሱም ጋር ካስታረቀን፤ እኛም እርስ በርሳችን ከወንድሞቻችን ጋር መታረቅ ሊያቅተን አይገባም። ይልቁን አሁን በጥላቻ እሳት ሀገራችን እየነደደች ባለችበት፣ ወንድም ወንድሙን በሚገድልበት በዚህ ሰዓት ከማንም በላይ ዕርቅ ለእኛ ያስፈልገናልና ክርስቶስ በሞቱ እንደታረቀን ሁላችን ልታረቅ ይገባናል።

3ኛ. ዮኅናት ምልክት ነው፤

በምድርም በሰማያት ሳሉ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ።

መስቀል ኀይላችን ነው!

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዝ የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል” በማለት በኀጢአት ምክንያት ስላጣነው ነፃነት፣ በእኛም ላይ ስለነበረ ዕዳና ባርነት ተናግሯል (ቈላስ. 2፥14) ። ይህ ባርነት የተወገደው፥ ነፃነትም ያገኘነው በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም ነው። ቅዱስ ያሬድ በመስቀሉ ስለተገኘ ነፃነት ሲናገር “ነቅዐ ሕይወትነ ኮነ ክርስቶስ ፍስሓነ ለእለ አመነ በደሙ ክቡር ቤዘወነ በኀይለ መስቀሉ ኮነ ግዕዛነ ÷ ደስታችን ክርስቶስ የሕይወታችን ምንጭ ኾነ፤ ለአመንነው በክቡር ደሙ ተቤዣን፤ በመስቀሉ ኀይል ነፃነት ሆነ” ብሏል።

እንደዚሁም “እግዚአብሔር ተአኵተ ወሰብእ ግዕዘ ወሰይጣን ተአሥረ በኀይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ÷ በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኀይል እግዚአብሔር ተመሰገነ፤ ሰው ነፃ ወጣ፤ ሰይጣን ታሰረ” በማለት በክርስቶስ መስቀል ስላገኘነው ነፃነት ሰብኳል። ምክንያቱም በኀጢአት ምክንያት ያገኘን ባርነት የተወገደው በደመ መስቀሉ ነውና። ስለሆነም በክርስቲያኖች ዘንድ መስቀል የነፃነት ምልክት ሆኗል። በዓለ መስቀልን የሚያከብር ክርስቲያንም በደመ መስቀሉ ነፃ መውጣቱን እየሰበከ ነውና የክፋት፣ የዘረኝነት፣ የጥላቻና መሰል ኃጣውእ ባርያ እንዳይሆን ሊጠነቀቅ ይገባዋል።

ሃኖ, ቲውስ ያገኘንበት ነው፤

የሰው ልጅ በአዳም ኀጢአት ምክንያት ካገኘው ሞት የሚያድነው፥ ከሕመሙም የሚፈውሰው አዳኝ ይፈልግ ነበር። አዳም ባለመታዘዝ የቈሰለው ቍስል በእንስሳትም ሆነ በቅዱሳን ነቢያት ደም የሚፈወስ አልነበረምና፥ የእግዚአብሔር ልጅ የአዳምን ቍስል ቈስሎ ይፈውሰው ዘንድ ሰው ሆነ። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ “ወበእንተ ኃጣውኢነ ውእቱ ተሰቅለ ዲበ ዕፅ በሥጋሁ ከመ ያውዕአነ እምኀጣውኢነ ወበቍስሉ ያሕይወነ። እስመ በቍስለ ዚአሁ ሐየውክሙ ቍስለክሙ እንዘ ከመ አባግዕ ትሳኰዩ- ከኀጢአታችን ያወጣን ዘንድ፥ በቍስሉም ይፈውሰን ዘንድ እርሱ ስለ ኀጢአታችን በሥጋው በእንጨት ላይ ተሰቀለ፤ በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ፤ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና።” በማለት በደመ መስቀሉ ስላገኘነው ፈውስ አስተምሯል። (1ጴጥ. 2÷25)

ቅዱስ ያሬድም “ወበመስቀሉ አርኃወ ገነተ፤ ወበመስቀሉ ገብረ መድኃኒተ÷ በመስቀሉ ገነትን ከፈተ፤ በመስቀሉም ፈውስን መድኀኒትን አደረገ” በማለት በመስቀሉ መድኀኒትና ፈውስ እንደተደረገ ተናግሯል። የቅዱስ መስቀሉ መድኀኒትነት ምንጩ ክርስቶስ ነው። በጌታችን ልደት የእግዚአብሔር መልአክ “...ተወልደ ለክሙ ዮም መድኀን ዘውእቱ ክርስቶስ እግዚእ ቡሩክ በሀገረ ዳዊት-ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ ተወልዶላችኋል” ብሎ ክርስቶስ ሊፈውሰን የተወለደ መድኀኒት እንደሆነ ነግሮናል (ሉቃ. 2፥11)።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም “ሞገስነ ወክብርነ ቀርነ መድኀኒትነ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ÷ ሞገሳችንና ክብራችን፥ የድኅነታችንም ቀንድ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” ብሎ አመስግኗል። ቤተ ክርስቲያናችንም መስቀሉ ፈዋሽ ነው፤ የፈውስም ምልክት ነው ብላ የምታስተምረው፥ ዓለም ከቍስሉ በተፈወሰበት በክርስቶስ ደም ስለተቀደሰ ነው። ስለሆነም እንደ ሀገር ከታመምንባቸው በርካታ ጉዳዮቻችን እንድንፈወስ የመስቀሉን ዓላማ መከተል ያስፈልገናል።

በአጠቃላይ ቅዱስ መስቀል ሰላም የታወጀበት፣ ዕርቅ የተፈጸመበት፣ ከባርነት ነፃ የወጣንበትና የተፈወስንበት የሰላምና የፍቅር የአንድነትም ምልክት ነውና፥ በዓለ መስቀሉን ስናከብር ከልዩነት ይልቅ አንድነትን፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅርን በመምረጥ ለሰላም የሚከፈል የትኛውንም ዋጋ በመክፈል ሰላምን ልንከተል ይገባል። ለዕርቅም የተዘጋጀ ልብ ይዘን ያጣነው ሰላማችንን ለማግኘት፣ የጠፋው አንድነታችንና ፍቅራችን ለመመለስ ተግተን ልንሠራ ይገባናል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደመ መስቀሉ የሰጠን ሰላምና የፈጸመው ዕርቅ ለሕዝብ ለአሕዛብ ሳይባል ለዓለም ሁሉ የተደረገ ነውና፥ በመስቀሉ የተከፈለለትን ዋጋ የሚያውቅና በክርስቶስ ስም የተጠራ ክርስቲያን ወደኋላ ተመልሶ በዘርና በቋንቋ ሊከፋፈል፣ ሊጠላላና ሊገዳደል ፈጽሞ አይገባም፡ ፡ ስለሆነም ክርስቶስን እንመስል ዘንድ ተጠርተናልና ለሰላምና ለዕርቅ ቅድሚያ ልንሰጥ፥ ለተግባራዊነቱም ተግተን ልንሠራ ይገባናል።

ስለዚህ የሰላምና የዕርቅ ምልክት የሆነውን መስቀል በአንገታችን አስረንና በሰውነታችን ተነቅሰን ሳለ፦ ሰላምን ጠልተን፥ ዕርቅ ሸሽተን በጥላቻና በዘርኝነት፥ በመገፋፋትና በጦርነት የምንኖር ከሆነ፥ የመስቀሉን ዓላማ ዘንግተናልና ከወደቁት እንደወደቅን ልናስብ ይገባል። የመስቀሉን ዓላማ ዘንግተን ከክርስቶስ አፍ ተተፍተን መቅረባችን ከእኛ እንዳይወሰድ ወደ ቀደመው ፍቅራችን ልንመለስ፥ ሰላምን ልንሻትና ልንከተላት ይገባል። አምላክ ቅዱሳን በደመ መስቀሉ የተደረገው ሰላምን እንድንከተል በፍቅርም እንድንኖር ይርዳን። (መዝ. 33÷14)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በምድርም በሰማያት ሳሉ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ።

መስቀል ኀይላችን ነው!



በምድርም በሰማያት ሳሉ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ።



"ኢትዮጵያንና ሳባን ለአንተ ቤንታ ሰጥቻለሁ።"

(ኢሳ. 43፥3)

በቀሲስ ያሬድ ክብረት
የሊቃውንት ጉባኤ አባል

መስቀል ኀይላችን ነው!

1. መግቢያ

ስጦታ ከሁሉ በላይ ለሆነ የመልካም ግንኙነት የፍቅርና የክብር መግለጫ ለወደዱትና ለአከበሩት አካል ልዩ የልብ ስፍራም እንዳለው ተግባራዊ ማረጋገጫ ነው። ለሰጪውም ለስጦታ ተቀባዩም በተሰጣቸው ዘመን ሁሉ ለራሳቸውና ለትውልዳቸው ያለፈውን ለታሪክ፥ ያለውን ለልብ ሐሴትና ለሚመጣውም የበረከት ማግኛ የቃል ኪዳን መጠበቂያ ምነው። በመካከላቸው የሚሰጠው ስጦታም ከስጦታዎች ሁሉ የተለየ የተመረጠ እና የከበረ ስፍራ ያለው ግምቱም ከስጦታነት ያለፈ ትርጉም ያለው ነው። ይህ ስጦታ የሁሉ አስገኝና ባለቤት ከሆነው ከእግዚአብሔር አምላክ ሲሆን ደግሞ አቻ የማይገኝለት ይልቁንም ለልዩ የኀላፊነት ዓላማ መመረጥ እንደሆነ ማሳያ ነው። በአብርሀም ቃል ኪዳን ሕዝበ እስራኤልን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ (ዘፍ.17፥1-21) እንደምንለው ሁሉ፥ ኢትዮጵያንና ሳባን ደግሞ በረከትን አጥብቆ ወዳድ ለሆነው፥ በዚህ ጽናቱም ስሙ እስራኤል ተብሎ የተለወጠና ለዐሥራ ሁለቱ ነገድ አባት ለሆነው ለያዕቆብ (ለእስራኤል) የፋንታነት የቃል ኪዳን ስጦታ አድርጎ የሰጠበት አምላካዊ ሕያው ቃል ነው። ፋንታ ድርሻ ማለት ሲሆን፤ የፋንታነት ስጦታ ኢትዮጵያና ሳባ የስጦታው ሰጪና ተናጋሪ እግዚአብሔር የስጦታው ተቀባይ የአብርሀም የልጅ ልጅ ያዕቆብ ነው ማለት ነው።

በእርግጥ የኢትዮጵያ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ አርእስተ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ተነሥቷል። በዚህ አጭር ጽሑፍ ከተነሣንበት ርእስ አንጻር ከእምነታና ሥርዐተ አምልኮዋ ታሪካዊ መሠረት ጋር በጥቂቱ በመዳሰስ በፋንታነት የተሰጠንበትን ልዩ ስጦታነትና ያለንን ስፍራ በማወቅ፥ የተሰጠንን ሀብተ እግዚአብሔር በመጠበቅ የድርሻችንን እንድንወጣ ለማስታወስ ነው። ይህን ፈንታነት በመረዳት እንደ ሀገር ጥንት የብሉይ ኪዳንን ሥርዓተ አምልኮ በመፈጸም አምልኮተ እግዚአብሔርን አጽንቶ ሥርዐተ ሃይማኖትን ጠብቆ በሀገር በቀል ዕውቀት ትውፊታዊ፥ መንፈሳዊ ሥርዐትንና ሀገራዊ ዕሴትን ገንብቶ ሁለንተናዊ ሥነ ምግባርን ለትውልድ ያስተማረች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነች።

ይሁን እንጂ አሁን በአለንበት ዘመን የያዙትን እምነት ወይም አመለካከት በበቂ አመክንዮ ማስረዳትና አእምሮን መማረክ ያቃታቸው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እምነት፥ ታሪክ፥ ሥርዓተ አምልኮና ሁለንተናዊ አስተዋጽኦዋ ሙያዊ ሐሳብና ትንታኔ የሰጡ በማስመሰል ወይም የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም አመክንዮ አልባ አሉታዊ ትርክቶችን በመንዛት የሀገርንም የቤተ ክርስቲያንንም ታሪክና እውነት ተረት ተረት በማስመሰል የሚቃረኑም አልጠፉም። ይህ ከንቱ ሐሳባቸው ትውልድን እንዳይበርዝ እውነትን የመግለጥና የማስረዳት ግዴታችን ስለሆነ፥ የተሰጣትን ሰማያዊ ተልእኮ በመወጣት ሀገርን የገነባች መሠረታም የጸናው በሰው ሐሳብ ሳይሆን ሕያውና ዘለዓለማዊ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያንና ሳባን ለአንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ እንዳሉ፥ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን እንደ ሀገር በሕዝብነትና በሀገር መሪዎች እንዲሁም በግለሰብ ደረጃም የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ የማዳን ጥበቡን የመሻትና በአምልኳቸውም ከእርሱም ዕድል ፋንታን ለማግኘት የነበራቸው ጽናትና በእምነት አርአያነታቸውም ያለንን ስፍራ ማውሳት ተገቢ ነው። ስለዚህ ከበዓለ መስቀል ዓውድ አንጻር ስለ ነገረ ድኅነታችንና የድኅነት ምልክቶቻችን ስለሆኑት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ቅዱስ መስቀል እንዲሁም በፋንታነታችን የተሰጠንን ሀብተ እግዚአብሔርና በተሰጠንም የልጅነት ጸጋ ለመጽናት ምን ማድረግ እንዳለብን በጥቂቱ እንዳስሳለን።

2. እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያሰጠው ፍጹም ፍቅርና ያሚደነ ሥራ

ነቢዩ አሳይያስ የትንቢቱን ቃል ሲጀምር.... “እግዚአብሔር ተናግሯልና ሰማያት ስሙ፥ ምድርም አድምጪ፥ ልጆችን ወለድሁ፤ አሳደግሁም፤ እነርሱም ዐመፁብኝ” በማለት ስለ ቃል ኪዳኑ ሕዝብ የእስራኤልን ዐመፃ እንዲሁም በተፈጥሮው የቅድስናና የክብር የልጅነት በኩርነቱ ላይ ያመፀውን የአዳምን በደል የምድርንና የሰማይን ምስክርነትን ይጠራል። የሰው ዘር ሁሉ በዚህ ዐመፃ ቢሄድ የሚገጥመውን ጉዳት ሲገልጽ የእግዚአብሔርን የድኅነት የአዋጅ ድምፅ ያልሰሙትን የሰዶምንና ገሞራን ጥፋት በማውሳት (ዘፍ 19፡1-28)“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን፥ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር» አለ። እንዲሁም «እናንተ የሰዶም አለቃዎች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ እናንተ የገሞራ ሕዝብ ሆይ፥ የአምላካችንን ሕግ አድምጡ” (ኢሳ. 1፥9፡10) በማለት ያውጃል። እንደ ሰው ልጅ በደል ሳይሆን እንደ አምላካዊ ይቅርባይነቱ እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጅ ያለውን ፍቅርና መለኮታዊ የማዳን ሥራ፥ ስለ አስቀረልን ዘርም “ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች” (ኢሳ. 7፥14) በማለት የተናገረው የትንቢት ቃል ፍጹም ሆኖ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን ሲያረጋግጥ በመልአከ ብሥራት፦“... ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ... ክብር

ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ” የሚል ታላቅ ዝማሬ ተሰማ (ሉቃ 2፥11-14)።

በዚህም ሰማይና ምድርም የሰው ልጆች ስለፈጸሙት በደል ብቻ ሳይሆን በፍጹም ተዋሕዶ አምላክ ሰው ሰውም አምላክ በመሆኑ ድንቅ ምስጢር ስለተደረገላቸው ይቅርታና ምሕረት ለታላቁ ደስታና የምሥራች ጭምር ለምስክርነት ተጠሩ። በዚህ ምክንያት ያ የዓመፃ ዘመን በሰው ኀጢአት ምክንያት የነበረው የፍዳ ዘመን ዓመተ ዓለም አክትሞ የምሕረት አዋጅ “ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ” (ማር. 1፥14፡15) እያለ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ የድኅነትን የዐዋጅ ቃል አወጀ። “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል።” (ዮሐ 3፥15፡16) በማለት አምላካዊ ፍጹም ፍቅሩንና የማዳኑንም ሥራበመስቀል ፈጸመ።

ልበ አምላክ ዳዊት “ወገብረ መድኀኒተ በማእከለ ምድር፥ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ” (መዝ. 73፥12-14)፤ እንዲሁም “ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው” (መዝ. 59፥4) እንዳለ፥ ከዘመናት በኋላ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለአዳም የሚድንበትን ወደ ቀደመ ክብሩና ርስቱ የሚመለስበትን አዘጋጀ። ይህም ከሞት ቀስተኛው ከቀደመው ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ የሞት ቁራኝነት ያመለጥንባቸውን የድኅነት ምልክት ቅድስት ድንግል ማርያምና ቅዱስ መስቀል ናቸው። ከፍጥረት ወገን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ዘለዓለማዊና መለኮታዊ የማዳን ጥበቡን የፈጸመባቸው ያከበራቸውና የሰውን ልጅም ክብር ያሳየበት ወደ ቀደመ ክብርና የቅድስና ስፍራውም የመለሰባቸው ናቸው።

በሰይጣን ተንኮል ሞትን አትሞቱም በሚል የእባብ ምክር፥ በቀዳማዊ አዳም በቀዳሚት ሔዋንና በዕፀ በለሲቱ ምክንያት ርስቱንና ክብሩን በአጣባቸው መንገድ ወደ ቀደመ ማንነቱ መመለስ አለበትና፥ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ከዳግሚት ሔዋን ቅድስት ድንግል ማርያም በፍጹም ተዋሕዶ በነሣው ሥጋ በቅዱስ መስቀል ላይ ተሰቅሎ የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ርስቱ ተመልሷል። በቀዳማዊ አዳም ምክንያት ወደ ሰው ሁሉ የደረሰው ኀጢአትና ሞት በኋለኛው አዳም በኩል በክርስቶስ አማካይነት ለሰው ልጆች ጽድቅና ሕይወት ተገኝልን። (ዮሐ. 1፥12፤ ሮም 5፥12-21፤ 1ቆሮ. 15፥22፥45)

ሌላውን ሕያው ለማድረግ የአዳምን ሞት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደሞተ ሁሉ፥ ከሕይወት ዛፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘው የሕይወት ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስን የተመገበ ሁሉ ደግሞ በሕይወት ይኖራል። ለዚህም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም “...ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከእኔ የተነሣ ሕያው ሆኖ ይኖራል” (ዮሐ. 6፥54-56፥ 11፥25) ሲል የተናገረው፥ ከእርሷ የነሣውን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው። ይህን ስናደርግ ደግሞ በሕይወት እንኖራለን፥ ሕያው ነውና ሕያዋን ያደርገናል በዚህም ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን መውረሻ፥ ጠላትን ድል መንሻ ሆነን ማለት ነው። በመስቀሉም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ ራሱን ለዓለም የሰጠበት ታላቅ የድኅነት ዙፋን ነው (ሉቃ. 22፥14-23፤ ዘጸ. 17፡5-8፤ ዕብ 9፡4)። ስለዚህ መስቀል የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት፥ የኀጢአት ይቅርታ የተገኘበት፥ ነፃነት የታወጀበት፥ ጨለማ የተሸነፈበት፥ ደኅንነት የተረጋገጠበት እንዲሁም ዘለዓለማዊ ሕይወት የተገኘበት፥ የነፍስ የሥጋ ድኅነት የተሰጠበት ስለሆነ እናከብረዋለን። ከኀጢአት ባርነት ነፃ የወጣንበት የክርስቶስ የሞትና የትንሣኤ ምልክት፥ የክርስትናችን አርማም ስለሆነ እንመካበታለን። በድኅነት ምልክትነቱም ከደዌ ሥጋና ከደዌ ነፍስ እንፈወስበታለን፤ ጠላት ዲያብሎስን እናሸንፍበታለን፤ በረከትንም እናገኝበታለን።

3. ይህ ከኢትዮጵያ እና ከሳባ ጋር ምን ያገናኘዋል?

እግዚአብሔር በምድርም መካከል መድኀኒትን የአደረገበትን፥ የእባቡንም ራስ የቀጠቀጠበትን ቅዱስ መስቀልና ቅድስት ድንግል ማርያምን ሲያዘጋጅ ለኢትዮጵያም ሰዎች ምግበ ነፍስንም ሰጥቷል (መዝ. 73፥12-14)። ይህ በአጋጣሚ ሳይሆን በአምላክ ዕቅድ ውስጥ ያለ በመሆኑ፥ ማኅደረ እግዚአብሔር የነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት (ታቦተ ጽዮን ፥ ጽላተ ሙሴ) መኖር በሀገር አቀፍ ደረጃ የመካነ ጽላት መገኛና ምግበ ነፍስ የሆነው ስብሐተ እግዚአብሔር ማድረሻ ሆነ። በምክንያተ ድኂን ማኅደረ ቃል አማናዊት ጽዮን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መናገሻ፥ የቅዱሳን መክበሪያ ሀገር ሆነ። በዚህም ለሕዝቡ የበረከት ማግኛ፥ መንፈሳዊና ማኅበረሰባዊ ጤንነቱ የተጠበቀ ትውልድ መፍጠሪያ መሆኑ የማይታበል ነው። በተጨማሪም ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀሉ ኢትዮጵያ የተገኘበት አጋጣሚ የፈጠረው ታሪካዊ ክሥተት ሳይሆን ፈቃደ እግዚአብሔር ነው። በሀገራችን በመገኘቱም በሃይማኖታዊና ባህላዊ የአኗኗራችን መስተጋብር ውስጥ የመስቀል ሀገር አቀፋዊ ክብር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታን ያተረፈ እንደሆነም አሁን የምናከብረው ዘመን ተሻጋሪው በዓለ መስቀል በቂ

መስቀል ኀይላችን ነው!

ማስረጃ ነው። ይህም በፈንታነታችን የተሰጠን አምላካዊ ስጦታችን ነው።

በሀገራችን ታሪክ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ያለን የጠነከረ ሥነ ልቦናዊና ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ የአኩሪ ታሪክ ባለቤት የመሆን ምስጢር ነው። ይህንንም እውነተኛ የታሪክ ጸሓፊዎችም የሚሰጡት ምስክርነት ነው። በዚህች ምሥጢር በሆነች ሀገር የምንኖር የዛሬው ትውልድም የሥነ ልቦና የበላይነት፥ የአሸናፊነት መንፈስና ለፍትሕ ለርትዕ ያለን ወኔ የተሠራበት የልቦና ውቅር መሠረቶች መካከል አንዱ ነው። ዛሬ ላይ ኢትዮጵያን ታላቅ እናደርጋለን ብለን ስንነሣ ታላቅ የነበረችበት ዘመንና ሁኔታዎች ምን ይመስል እንደነበር የታላቅነቷን ምሥጢርና ታሪክን መመርመር ያፈልጋል። በታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች በከፍታ ደረጃ የሚያስቀምጥ የኢትዮጵያንም ሕዝብ የሥነልቦና ልዕልና ከሚያወሱት መካከል መጽሐፈ ክብረ ነገሥት አንዱ ነው። በይዘቱም የኢትዮጵያን ከፍታና ልዕልና፤ ኢትዮጵያውያንም በአምላክ የተመረጡ ሕዝቦች መሆናቸውን፤ እግዚአብሔር የምድር ዙፋኑን ከእስራኤል ለኢትዮጵያ እንደሰጠ የሚተነትን፤ ስለ ታቦተ ጽዮን፥ ስለ ንግሥተ ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን፥ ስለ ቀዳማዊ ምኒልክና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች የሚተርክ ድንቅ መጽሐፍ ነው።

ይሁን እንጂ የራሷን ትታ የሰው... እንደሚባለው፥ ከጥንት አባቶቻችን ከወረስነው ታሪክ፥ ትውፊትና ሥርዐት ይልቅ ለታሪካችን የባዕዳንን ምስክርነት ፈላጊዎች እየሆን ነው። በአካል ሊገዙን ላልቻሉ የሥነ ልቦና ተገዢ በመሆን እነርሱ የነገሩን ሁሉ እውነት እንደሆነ እንድናምን፥ ያለንን ነባር ታሪክና እሴት ዋጋና ክብር እንዳንሰጥ የሚያደርጉን ኩነቶች የዘመናችን ተግዳሮቶች ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎን ታሪክ መሥራት ባይችሉ አንኳን ታሪክን በመጠበቅና በማክበር ፈንታ ይልቁንም የባዕዳንን ሐሳብ የገዙ ልሂቃን ነን ባዮችም ጥቂቶች አይደሉም። በዚህም ያለምንም አመክንዮ የትናንት ወቃሾች አዲስ የቅገሮት ታሪክና ትርክት በመፍጠር በማኅበራዊ ሚዲያዎች ጭምር የሚያስተላልፏቸው ሰንካላ ሀሳቦች የሀገርን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትንና የሥነ ልቦና ጠንካራነትን የሚሸረሽሩ፥ እንዲሁም የእምነት ተቋምነት ክብርን የሚጋፉ ግለሰባዊ ተምኔቶች የበዙበት ነው። በመሆኑም ከግለሰባዊ አስተሳሰቦችና ምኞቶች ይልቅ እንደ አንድ አማኝ በእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት ቆመን ራችንን መመዘንና ሕዝበ እግዚአብሔርነታችንን በማጽናት ሀገርን፥ እውነትንና ትውልድን መጠበቅ ያስፈልጋል።

በራስ የማንነት ታሪክ ውስጥ ጥያቄ በማንሣት ኢትዮጵያዊነትን ለመገዳደር መሞከር ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለ ሳባ፥ ስለ ሀገራችን ስያሜም ሆነ ስለ ሳባ ፊደላችን አለማወቅ፥ በዚህ ስም የሚጠራና በዚህ ፊደል የሚገለገል እንዲሁም አምልኮተ እግዚአብሔርን በዚህ መልክ የሚፈጽም የሌለ እንደሆነም አለመረዳት ነው። በመሆኑም በእግዚአብሔር ሕያው ቃል የተገለጸው ይህንኑ እውነት ሊያጠናክር የሚችል ካልሆነ በቀር ሌላ አዲስ ነገር ሊያመጣ የሚችል ማንም እንደሌለ እናምናለን። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሚናገርባቸው መንገዶች አንዱ መጽሐፍ ነው (መዝ. 86፥6)። በዚህም አምላካዊ ሐሳቡን፥ ፈቃዱን፥ ዓላማውንና ዘለዓለማዊ ምሥጢሩን ለሰው ልጆች የሚያሳውቅበት ነው። እነርሱም እንደፈቃዱ ለመኖር የሕይወት መመሪያ አድረገው የሚጠቀሙበት ትውልዳቸውም የሚመራበት የሕይወት መንገድ ነው። "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል፤ ይከናወንልሃልም" (ኢያ. 1፥8) እንዳሉ፥ ይህ የሕዝበ እግዚአብሔር መመሪያ የሆነው ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ኢትዮጵያና ሳባም ፋንታነት ምን ተናገረ? በፋነታነታችንስ ከሌላው በተለየ ምን አገኘን? የሚለውን እንዲህ እናያለን።

ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ "አሁንም ያዕቆብ ሆይ፥ የፈጠረህ፥ እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ። በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም። እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኀኒትህ ነኝ፤ ግብፅን ለአንተ ቤዛ አድርጌ፥ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ። በዐይኔ ፊት የከበርህና የተመሰገንህ ነህና፤ እኔም ወድጀሃለሁና ስለዚህ ሰዎችን ለአንተ አሕዛብንም ለነፍስህ እሰጣለሁ" አለ። (ኢሳ. 43፥1-4)። ነቢዩ ዳንኤልም "ጥበብና ኀይል ለእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይባረክ፤ ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፤ ነገሥታትን ያፈልሳል፤ ነገሥታትንም ያስነሣል፤ ጥበብን ለጠቢባን፥ ዕውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል" (ዳን. 2፥22-23) ብሎ እንደተናገረ፥ ከእግዚአብሔር የሆነውን የመዳንን ጥበብ ያወቁ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን እንደ ሀገር፥ እንደ መሪ እንዲሁም እንደ ግለሰብ እግዚአብሔርንና ጥበቡን የመሻት፥ አጥብቆ የመፈለግ ሕይወት ነበራቸው። ይህም እርሱ በሰጠው የፈንታነት ድርሻም የቃል ኪዳን ሕዝብነት ማረጋገጫ ነው። በዚህም የታሪክ፥ የእምነትና የትውፊት

ቅብብሎሽ ዛሬም ድረስ ከእግዚአብሔር የሆነውን ሕያውና ዘለዓለማዊ ድኅነት በሚገኝበት በእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት (2ጢሞ. 3፥14-17) ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በተሰጣት የዘመን ተልዕኮና ፈንታም ትውልድን እያነጸች ለሰማያዊ ርስት ታዘጋጃለች።

ከእነዚህም ቅዱሱ መጽሐፍ በተምሳሌትነት ከገለጻቸው መካከል ሁለቱ ጃንደረቦች ከዓበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ነቢዩ ኤርምያስ በነበረው የነቢይነት ተልዕኮ በደረሰበት ግፍና ጉስቁልና በጉድጓድ ተጥሎ በነበረበትም ጊዜ በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ስለ ኤርምያስ በንጉሡ ፊት ፍትሕ የጠየቀ፥ በረኃብም እንዳይሞት የመገበ፥ በገመድ ጐትቶ ከጉድጓድም ያወጣው ነው። በዚህ ተግባሩም ከእግዚአብሔር ፈጽሜ አድንሃለሁ በእኔ ታምነሃልና ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፥ በማለት የድኅነት ዋስትና ተሰጥቶታል (ኤር. 38፥7-13፤ 39፥15-18)። በሐዲስ ኪዳንም የነቢዩን የኢሳይያስ መጽሐፍ ሲያነብ የነበረውን ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ ስለነበረውና በፊልጶስ ሐዋርያነት ክርስትናንና የነገረ ድኅነት ምስጢርን ተረድቶ አምኖ ስለተጠመቀው ባኮስ ይመሰክራል (ሐዋ. 8፥26-38)። ከዚህ የምንረዳው በብሉይም በሐዲስም እግዚአብሔር አምላክ በመለኮታዊ በማዳን ምሥጢሩ ውስጥ የምሥጢር ተካፋይ የሆንን በያዕቆብ የፈንታነት ድርሻችንም ልዩ ስፍራ እንደነበረን ማሳያ ነው።

3.1. ኢትዮጵያ

- ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች። (መዝ. 67፥31)
- በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፥ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፤ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፤ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ።ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል። (መዝ. 71፥9-11)
- እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል መድኀኒትን አደረገ፤ አንተ ባሕርን በኀይልህ አጸናሃት፤ አንተ የእባቦችን ራስ በውኃ ውስጥ ሰበርህ፤ አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ፤ ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው። (መዝ. 73፥13-14)
- በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፥ የቀረውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሶርና ከግብፅ፥ ከጳትሮስና ከኢትዮጵያ፥ ከዔላምና ከሰናዖር፥ ከሐማትም ከባሕርም ደሴቶች ይመልስ ዘንድ ጌታ እንደገና እጁን ይገልጣል። (ኢሳ. 11፥11)
- እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፦የግብጽ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረዣሞችም የሳባ ሰዎች ወዳንተ ያልፋሉ፤ ለአንተም ይሆናሉ፤ እጆቻቸውም ታስረው ይከተሉሃል፤ በፊትህም ያልፋሉ። ለአንተም እየሰገዱ፦ በእውነት እግዚአብሔር ባንተ አለ፤ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም ብለው ይለምኑሃል። (ኢሳ. 45፥14)
- የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን ይላል እግዚአብሔር (አሞ. 9፥7)
- የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ፤ የምድያም ሀገር መጋረጃዎች ተንቀጠቀጡ። (ዕንባ. 3፥7)
- በዚያን ጊዜም አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሕን ልሳን እመልስላቸዋለሁ፤ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፥ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቍርባኔን ያመጡልኛል። (ሶፎ. 3፥10)
- ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶነ በር። (ሐዋ. 8፥26-39)

3.2. ንግሥተ ሳባ

- ሳባ የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። (1ነገ. 10፥1)
- የሳባም ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ፥ ሠርቶትም የነበረውን ቤት፥ የማዕዱንም መብል፥ የብላቴኖቹንም አቀማመጥ፥ የሎሌዎቹንም አሠራር፥ አለባበሳቸውንም፥ ጠጅ አሳላፊዎቹንም፥ በእግዚአብሔርም ቤት የሚያሳርገውን መሥዋዕት ባየች ጊዜ ነፍስ አልቀረላትም። (1ነገ. 10፥4፤ 2ዜና. 9፥3)
- ለንጉሡም መቶ ሃያ መክሊት ወርቅ፥ እጅግም ብዙ ሽቱ፥ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው። የሳባ ንግሥት ለንጉሡ ለሰሎሞን እንደሰጠችው ያለ የሸቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም ነበር።

መስቀል ኀይላችን ነው!

(1ነገ. 10፥10፤ 2ዜና 9፥9)

- የሳባም ንግሥት የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በግመሎች ላይ ሽቱና ብዙ ወርቅ፥ የከበረምዕንቍ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋራ ሰሎሞንን በኢየሩሳሌም በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። ወደ ሰሎሞንም በገባች ጊዜ በልቧ ያለውን ሁሉ አጫወተችው (2ዜና. 9፥1)

- የሳባም ንግሥት ወደ ንጉሡ ካመጣችው የሚበልጥ ንጉሡ ሰሎሞን የወደደችውን ሁሉ፥ ከእርሱም የለመነችውን ሁሉ ሰጣት። እርሷም ተመልሳ ከባሪያዎቿ ጋራ ወደ ምድሯ ሄደች (1ነገ. 10፥13፤ 2ዜና. 9፥12)

- በምዕራብ ደሴትም የሚኖሩ የኖባና የህንደኬም፥ የሳባ የኢትዮጵያና የግብፅም ሰዎች በእነሱ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ምድርና ሰማይን የምገዛ፥ መወደድንና ክብርን የምሰጥ፥ የማድንና የምገድልም እግዚአብሔር እኔ እንደሆንኩ የዚያን ጊዜ ያውቁኛል። (1መቃ. 34፥9)

- እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኀኒትህ ነኝ። ግብፅን ለአንተ ቤዛ አድርጌ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ። (ኢሳ. 43፥3)

- ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፤ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ። (ኢሳ 60:6)

- እግዚአብሔር ተናግሯልና ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁን በይሁዳ ልጆች እጅ እሸጣለሁ፤ እነርሱም ለሩቆቹ ሕዝብ ለሳባ ሰዎች ይሸጧችኋል። (ኢዮ. 3፥8)

- ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋራ ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ። (ማቴ. 12፥42፤ ሉቃ. 11፥31)

4. በቴንታነታችን የተሰጡን ምንድን ናቸው?

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ የፈጸመው የማዳን ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ ቢሆንም፥ በፋንታነት ልዩ ድርሻ አለን። ይህ ለራስ ማድላት ሳይሆን ቅዱስ መጽሐፍ የተናገረውን እውነት መሠረት በማድረግ ነው።በቅዱስ ቃሉ መጠቀስ የሚያስታብይ ሳይሆን እንደ ሀገርና የሰውነት ተልእኮ በእግዚአብሔር ሐሳብና ዓላማ ውስጥ ያለንን ስፍራ እንድናውቅ የሚያደርግ ነው። እንደ ፈቃዱ የተፈጠርንበትንና የተመረጥንበትን ዓላማ በመረዳት ኀላፊነታችንን እንድንወጣም ነው። ፋንታ ማለት ድርሻ ማለት ሲሆን ድርሻ ስንልም የእርሱ ፋንታ የሚደርሰው ለእርሱ የሚገባው አካል ማለት ነው። ስለዚህ ከተነሣንበት ርእስ ጭብጥ አንጻር እግዚአብሔር ሙሴን፦ "...ይህን ሕዝብ አየሁት፥ እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው፥ እንዳጠፋቸውም ተወኝ፤ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ" አለው (ዘፀ. 32፥9)። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ሕዝብ በእስራኤል ዐመፃ ምክንያት ሙሴን ለሌላ ታላቅ ለሆነ ሕዝብ መሪ እንደሚያደርገው ተናገረ። የቃል ኪዳኑን ሕዝብ እስራኤልንም ልዩ ድርሻ ካለው ሕዝብ ጋርም ሲያነጻጽር፦ "የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?" (አሞ. 9፥7) በማለት ስለ ኢትዮጵያ ልዩ የፋንታነት ድርሻ ተናገረ።

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸችበት መንገድ ልዩ ልዩ ቢሆንም፥ ከቃል ኪዳን ሕዝብነት አንጻር እስራኤል ለአብርሃም፥ ኢትዮጵያና ሳባ ደግሞ በፋንታነት ለልጅ ልጁ ለያዕቆብ የተሰጡ ሕዝበ እግዚአብሔር ናቸው። ከአምልኮም አንጻር በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የየራሳቸው ስፍራ ነበራቸው። ኢትዮጵያውያን ድርሻ እንዳላቸው ብቻ ሳይሆን ቅዱሳን አበው ሊቃውንትና ምእመናን አምልኮተ እግዚአብሔርን በልዩ መረዳት በሀገር በቀል እውቀት በማዳበር የሀገር ፍቅር ከሥነ-ምግባራዊ ሕይወት ጋር የተጣመረበት ነው። በዚህም ሰማያዊና ምድራዊ ሕይወትን በመጠበቅ መንፈሳዊና ማኅበራዊ መልካም የአብሮነት እሴቶች ከእለት እለት ኑሯችን ጋር ያላቸው ትስስር አንዱ መገለጫ ነው። በተጨማሪም በዚህ እምነትና እውነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ እምነት ተቋምነቷ በኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ የማይተካ ሚና ያላት መሆኑ ሁሌም የሚመሰከር እውነት ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊት፥ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት እንደ መሆኗ መጠን ሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን ከደረሰችበት የሥልጣኔና የዕድገት ደረጃ ከመድረሷ በፊት ፊደል ቀርጻ፥ ብራና ዳምጣል፥ ቀለም በጥብጣ ትምህርትና ሥልጣኔን ያስጀመረች፥ የፍትሕ ሥርዐትን በማስፈን በሥነ-ምግባርና በግብረገብነት የተጠበቀ ትውልድ በመፍጠር፤ የባዕዳንን ወረራና የሀገር ነፃነት በተደፈረም ወቅትም መንፈሳዊና አካላዊ ግንባር ቀደም

መሥዋዕትነትን በመክፈል፥ የቱሪስት መስሕብ የሆኑ ዘመን ተሻጋሪ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት፥ የዜማና የቅኔ ሀብት ባለቤት፥ በሥነ ጥበብ፥ በሥነ ሥዕል፥ በሥነ ጽሑፍ፤ በኪነ ሕንጻ፥ በአካባቢ ጥበቃ፥ በሥርዐተ ሕግ ቀረጻና ሀገራዊ ክብርንና ዕሴትን በማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና የተጫወተች መንፈሳዊት ተቋም ነች። በአጠቃላይ ሥነ-ጽሁፍ ከእነፊደሉ፤ ዘመንን ከእነቀመሩ፤ ነፃነት ከእነክብሩ፤ ሀገርን ከእነ ድንበሩ፤ ሀገራዊ አንድነትን ከእነጥብዓቱ ያስረከበች ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ለደረሰችበትና ከሌሎች ሀገራት በልዩነት በኩራት የምትመካባቸውን ሀገራዊ ሀብቶች በጠንካራ መሠረት ላይ የጣለች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ነች።

የዚህ ሁሉ የበረከት ውጤት መነሻው በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን የፋንታነት ስፍራና ምርጫ ነው። እግዚአብሔር አምላክ “እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ ... እኔ የምሠራቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከፊቴ ጸንተው እንደሚኖሩ፥ እንዲሁ ዘራችሁና ስማችሁ ጸንተው ይኖራሉ” (ኢሳ. 66፥2-22) በማለት ቃሉን ያጸና በመሆኑ በጸናው ስሙ ጸንተው ለኖሩ፥ ለያዕቆብም የፍቅር ስጦታ ለሆኑት፥ በብሉይና በሐዲስ ኪዳንም በዘመን ሁሉ ለፈለጉት፥ ቃሉንም ለማገልገል ዘወትር ለሚንቀጠቀጡለት ኢትዮጵያውያን በፋንታነት የቃል ኪዳኑ ታቦት (ታቦተ ጽዮን፥ ጽላተ ሙሴ)፥ ዓለምን ያዳነበት ግማደ መስቀል፥ “በዚያን ጊዜም አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሕን ልሳን እመልስላቸዋለሁ፤ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፥ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ፥ ቍርባኔን ያመጡልኛል” (ሶፎ. 3፥10) በተባለው መሠረት፥ በቅዱስ ያሬዳዊ ልዩ የምስጋና ልሳን ስብሐተ እግዚአብሔር ዘወትር የሚደርስባት፥ የቅዱሳን መካናት ማእከል፥ ቅዱሳን የሚከብሩባት፥ የአማናዊት ጽዮን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መናገሻ፥ ቅዱስ መስቀል የሚከብርባት፥ ሰማያዊ መንግሥቱን መውረሻ ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባትና ሌሎች ኢትዮጵያዊ የእምነት መንፈሳዊ ዕሴቶቻችን ሁሉ የተሰጡን በመሆናቸው በእምነትም በሕይወትም የምንረዳቸው እውነቶች ናቸው።

በእምነት ተቋምነት በዚህ ልክ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ታላላቅ ተግባራትን ፈጽሜያለሁ የሚል ማንም ቤተ እምነት እንደሌለ ለሁሉም ግልጽ ነው። ይህን ሠርቻለሁ ቀደምኪችሁ በማለት በዘመንም በተግባርም ቁጠራ ሳትገባ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ እንደ እናት ሆደ ሰፊ በመሆን እንደየነገዱ፥ እንደየእምነቱና አመለካከቱ በማክበር በአቃፊነት ስታገለግልም ኖራለች፤ እያገለገለችም ትገኛለች። ይሁን እንጂ ለዚህ ተግባሯ ምስጋናና ክብር በመስጠት ፋንታ በተገኙ አጋጣሚዎች በማይወክሏትና በማያውቋት አካላት አሉታዊ ፍረጃዎችን ጨምሮ የተቋምነቷን ህልውና በሚገዳደር መልኩ በልጆቿና ተቋማዊ ክብሯ ላይ የሚፈጸሙ ጫናዎችና የገጽታ ማበላሸቶች ሚዛን ያልጠበቁ ክሥተቶች እየሆኑ ነው። አልፎ ተርፎም ከእግዚአብሔር ሐሳብ የአገልግሎት ዓላማዋ ውጪ በዘመን ለተነሡ ያለፉ ሥርዐቶች አገልጋይ በማድረግ የሚነዙ ግለሰባዊ አለፍ ሲልም ተቋማዊ ጥላቻዎች የተለመዱ እየሆኑ መጥተዋል፡ ፡ ይህ ዘላቂ መፍትሔ የሚያስፈልገው ቢሆንም ይህ ከሰው ወገን ብቻ ሳይሆን በፈንታነታችን ድርሻ የምትሰጠውን አገልግሎት ለማደናቀፍ ከሰይጣን የመጣ የዘመን ፈተና እንደሆነ እንረዳለንና ነገረ መስቀሉን እያሰቡ በአገልግሎት መጽናት ያላትንም ዘመን ተሻጋሪ እውነት ለትውልድ መግለጥ ያስፈልጋል ማለት ነው።

5. ከንግሥተ አዜብ ፍርድ ለመዳን ምን እናድርግ?

ፍርድ ፍጹም እውነተኛ ፈራጅ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሚፈጸም ነው (ማቴ. 24፥36፤ ሐዋ. 17፥31)። በዘመን ፍጻሜ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፍርድ የሚፈጸመው የሰውን ልጅ ለማዳን በለበሰው ሥጋ የሚፈጸምና ፍርድም የማይቀር መሆኑንም “እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ ወአምላክነሂ ኢያረምም እሳት ይነድድ ቅድሜሁ ፥ አምላካችን በግልጥ ይመጣል ዝምም አይልም፤ እሳት በፊቱ ይቃጠላል” (መዝ. 49፥3) ይላል። በዚህም ሁሉንም እንደ ሥራው ዋጋውን ለመስጠት የሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ዋጋውን በሚቀበልበት የእውነት እሳት፥ የፍርድ እሳትም በሚነድበት ጊዜ በአምላክነቱ የፈጸመውን ድኅነት ለአላመኑና ላልተቀበሉት እንደ ሕዝብ የነነዌ ሰዎች፥ እንደ ግለሰብ የንግሥተ ሳባ በማያምኑና ምሕረቱን በማይፈልጉ ሰዎች ላይ የሚፈርዱት ፍርድ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላክነቱ የፈጸማቸውን ተአምራትና ድንቅ ምልክቶች አይሁድ እናምንብህ ዘንድ ሌላ ምልክትን ስጠን የሚለው ትልቁ ጥቂያቸው ነበር። እርሱም “ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም” (ማቴ. 12፥42፤ ሉቃ. 11፥31) ይልቁንም የነነዌ ሰዎችና ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል አለ።

የነነዌ ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ንስሓ ገብተው ሀገርን ከጥፋት ታድገዋል። ንግሥተ አዜብ የሰሎሞንን ጥበብ ልታይ የመጣችው የድኅነትና የጥበብ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ፍለጋ ነው። በእርሱም እምነቷ የጸና

መስቀል ኀይላችን ነው!

በመሆኑ ለሚያምኑ የሃይማኖት ምልክት፥ ለማያምኑ ደግሞ የፍርድ ምልክት መሆኗ በጌታ ቃል ተመሰከረላት። እርሱም ከዮናስ የሚበልጠው ዮናስን በነቢይነት የላከው የዮናስ ፈጣሪ፥ ከሰሎሞን የሚበልጠው ለሰሎሞን ጥበብን የሰጠ የሰሎሞን ፈጣሪ ነው። በዘመን ፍጻሜ የበደለውን ሥጋ ለብሶ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተ፥ የኀጢአትን ፍርድ ድል ነሥቶ በሞቱ ሕይወትን የሰጠ፥ በስሙ ለሚያምኑበት ደግሞ የልጅነት ሥልጣንን የሰጠን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው(ዮሐ. 1፥12)። እርሱም፦ "... ቃሌን የሚሰማ፥ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ" (ዮሐ. 5፥25) እንዳለ፥ የእግዚአብሔርን ድምፅ የምንሰማበት ጊዜ አሁን ነው። ልንጠነቀቅበት ከሚገባን የዘመናችን ፈተናና ፍርድንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጥ (ሮሜ 1፥21-28)፦

1. ሕይወት አልባ እምነት፡- እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ አምላክነቱ መጠን አለማክበርና አለማመስገን ውጤቱ ሐሳበ ከንቱነት፥ አለማስተዋል፥ ድንቁርናና ልበ ጨለማነት ነው።

2. አምላካዊ ክብርን መለወጥ፡- የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ዓለማዊና ቁሳዊ ክብር መለወጥ ውጤቱ ሰብእናን ማዋረድና ለርኩሰትም ተላልፎ መሰጠትነው።

3. ባዕድ አምልኮ (የእግዚአብሔርን ሐሳብ ማጣመም)፡- የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት፥ በፈጣሪም ፋንታ የተፈጠረውን ማምለክና ማገልገል ውጤቱ ለሚያስነውር ምኞት ተላልፎ መሰጠት፥ ያለ ተፈጥሮ ባሕርይም በፍትወት መቃጠልና የብድራትንም ዋጋ በራስ መቀበል ነው።

4. እግዚአብሔርን አለመፈለግ፡- እግዚአብሔርን ለማወቅ አለመፈለግና አለመውደድ ውጤቱ ለማይረባ አእምሮ ተላልፎ መሰጠት ነው፤ ይላል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ሁላችንን ከዚህ ፍርድ ለመጠበቅ ዘለዓለማዊ የማዳን ጥሪውንም፦ "እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ" (ኢሳ. 45፥22) እንዳለ፥ ወደ እርሱ ዘወር ስንል በለበሰው ሥጋ በመስቀል ላይ የከፈለልንን የደም ዋጋ የሰጠንንም የዘለዓለም ሕይወት እናያለን። በዚህም "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም። ተናግሬአለሁ አድኜማለሁ፤ አሳይቼማለሁ። በእናንተም ዘንድ ባዕድ አምላክ አልነበረም፤ ስለዚህ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ" (ኢሳ. 43፥11) ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት፥ የዓለም መድኀኒትነቱን በእርሱም ሕያዋን ፍጥረቶቹ እንደሆንም ምስክሮቹ ነን። አምላካዊ የማዳኑንም ሥራ የፈጸመባቸው መድኀኒትነቱንም ያረጋገጠባቸው የተሰጡን ምልክቶችም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ቅዱስ መስቀል በመሆናቸው የእምነት ምስክርነታችንም የጸና ነው። "ቤዛችሁ ቀርቧልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ" (ሉቃ. 21፥28) እንዳለ፥ ቤዛችን መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ለሰው ልጅ ፍጹም ድኅነትን የሰጠባቸው፥ መለኮታዊ ኃይሉን የገለጠባቸው ከፍጡራን ወገን ሁሉ ናቸውና ክብር በመስጠት ከአለማመን ፍርድ ራሳችንን እናንሣ። ኢትዮጵያና ሳባም የያዕቆብ የፋንታነት ስጦታዎች ስለሆንን በፋንታነታችንም የተሰጡን ዘለዓለማዊ የሕይወት በረከቶቻችንን እንጠብቅ፤ ስፍራችንን እንወቅ፤ በእምነታችንም ጸንተን እንኑር። ይህም ሲሆን ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን፤ ስማችንም በሕይወት መጽሐፍ ስለተጻፈ በስሙ ድል እንነሣለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!

The Cross is Our Power









September 26, 2026

EOTC Department of Public Relations

The Cross is Our Power

Prepared by EOTC Department of Public Relations
and Approved by EOTC Scholars Council

Table of Content

44 Editorial

46 Message of H.H. The Patriarch

49 Message of H.G. The General Manager

52 Message of Secretary General of the Holy Synod

55 Message of Deputy Manager of the Patriarchate for Spiritual Affairs

58 Message of Deputy Manager of the Economic and Social Sector

60 The doctrine of the cross

66 "The foundation of our firm hope is the cross." (2nd Pet. 1÷4; St. John Chrisostom)

Editor in Chief
Liqe Siyuman Eskindir Gebre Kristos

Edition
L.S. Nebiyu Eliyas

Graphic Design
Temesgen Tomas


Translation
Mhr. Akalewold Tessema (Ph.D.)
Miss Yordanos Addise

Photography
M.S. Abba Kiros Woldeab

Publisher
Tisaie Zegubaie Printing press

© September 26, 2026
Addis Ababa, Ethiopia

Editorial



The Cross is Our Power

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church annually commemorates the Feast of the Finding of the True Cross (Meskel) in public with great spiritual reverence, believing and teaching that the Cross is the symbol of salvation, victory, and liberation. When declaring "The Cross is Our Power," the Church affirms that this concept embodies deep spiritual, existential, and human meanings. In ancient times, the cross served as an instrument of horrific and humiliating punishment, considered the end for criminals, rebels, and the despised. However, through the precious price paid by Our Lord, God, and Savior Jesus Christ—Who was crucified on the Tree of the Cross for the death sentence imposed on us due to our transgressions-that instrument of execution was transformed into a eternal symbol of love, forgiveness, and victory. Our Lord, God, and Savior Jesus Christ was crucified on the Cross for our sins and transgressions, offering His Holy Body and shedding His Precious Blood to erase our certificate of debt. The Cross is the throne upon which Our Lord demonstrated His profound and boundless love for all creation. Through the blood of the Cross, the wall of enmity between God and humanity was torn down. As Saint Paul confirms, "But God forbid that I should boast except in the cross of our Lord Jesus Christ, by whom the world has been crucified to me, and I to the world" (Gal. 6:14), affirming that the Cross is the boast and foundation of life for Christians. The Cross became a crown of victory, a foundation of life, and a path of peace through the sacrifice Our Lord made on it for our salvation. According

to the canon and order of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, the Feast of Meskel is a great spiritual and cultural heritage. As we celebrate it, we must remember the faith and struggle demonstrated by Our Lady, the Holy Virgin Mary, the Holy Apostles, and the Martyrs. When the Jews buried the Holy Cross out of envy and instructed that heaps of refuse be piled over it to erase its whereabouts, Queen Helena, led by the Holy Spirit in the 4th century and guided by the elderly Kirakos, lit a bonfire (Demera) and added incense. The smoke rose up to the sky and bent down to point out the exact location of the Cross. To commemorate this historic event where she excavated the Cross from beneath centuries of rubbish, our Holy Church celebrates the Feast of Meskel Demera vibrant and publicly every year on Meskerem 16. The spiritual public festival of Meskel Demera is registered by UNESCO on the Representative List of the Intangible Cultural Heritage of Humanity. It stands as a great source of pride and treasure promoting Ethiopia to the world, serving as a tourism attraction that draws many foreign visitors and generates foreign exchange for our nation. Beloved Orthodox faithful! When celebrating the Feast of Meskel, our observance must not be limited to gathering around the Demera, lighting torches, and singing hymns. Beyond expressing the true spirit and meaning of the Cross in our daily lives, we must realize the importance of promoting the greatness of this festival in various languages using modern media tools, passing down its tradition intact to the next generation. As we reflect on the theology of the Cross (Negere Meskel), we ought to follow the path of forgiveness and life taught by Our Lord on the Cross when He prayed, "Father, forgive them, for they do not know what they do." For our country and people to live in peace, mercy, and love, Christians must be instruments of peace. Just as the vertical and horizontal beams meet to form one Cross, it serves as a bond of unity connecting the heavenly with the earthly, and human to human. We must set aside differences and support one another in the love of Christ—demonstrating Christ's love in practice by feeding the hungry, giving drink to the thirsty, clothing the naked, and comforting the grieving. Celebrating the Feast of Meskel must go beyond gathering in public squares, lighting bonfires, and singing joyfully; it requires writing the true meaning of the Cross upon our hearts. As we assemble for the Meskel Demera festival, we must reflect on the love Our Lord showed by surrendering His life, keeping His commandments, strengthening our faith, and praying earnestly for the peace and unity of our nation. The Cross becomes our power when we rely on its forgiving power when forgiveness feels difficult, when we recall its greatness to stand firm during trials, and when we follow its path of love by helping those in need.

May you have a blessed and peaceful Feast of the Holy Cross May the peace, love, and power of the Cross be with us all

Liqe Siyuman Eskindir Gebre Kristos

Head of the Public Relations Department of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church and General Manager of the Houses and Buildings Administration and Development Enterprise

Message of His Holiness the Patriarch



"The preaching of the cross is . . . the power of God;"

1 Cor. 1÷18

The Amharic literal meaning of the word cross is to be crucified, to be hang, to carry a lot of suffering; when our Lord was crucified on the cross, it means that He suffered this kind of suffering; in addition to suffering, the story of our Lord's crucifixion contains many mysteries of theology; the story of our Lord's crucifixion is started by suffering and completed by the pwer of life; in other words, the story of the cross starts with suffering, but the ends with salvation; since the final result of the cross is perfect salvation, it is right to emphasize salvation rather than suffering; "The true laughter is not the beginning, but the end" agrees with the story of the cross.

According to the general teaching of the Holy Bible, the preaching of the cross means "the preaching of suffering and salvation." Our Lord's suffering journey began as a child in exile and ended with death on the cross; (Matt. 2:13) Therefore, all the ups and downs of this long period are part of the preaching of the cross or the suffering on the cross.

The teaching of the gospel that our Lord taught during His ministry indicates that salvation is sealed by the cross, so salvation is part of the cross; it is also described as the preaching of the cross; when our Lord emphasized in the Holy Gospel the reason for His becoming a man, He said to us, "Son of Man came not to be ministered unto, but to minister, and to give his life a ransom for many." (Matt. 20:28)

Indeed, our Lord's being a man can be summarized in the two main messages; serving, and being a redeemer. His teaching, healing the sick, atoning for sinners, multiplying the bread and fish, raising the dead, etc., all indicate His ministry; and the suffering He received in His flesh and sacrifice done on the cross indicates His redemption; all these are parts of the cross.

The method of warfare that our Lord waged against sin, death, the grave, and the devil was based on spiritual, scriptural, and moral superiority; this nature and method of warfare is completely different from the warfare that we humans know and are accustomed to; the warfare that we know is to beat and kill the enemy with material weapons; but the warfare of our Lord is to captivate the minds of men, to persuade them, and to fulfill the requirements of the law, and to deprive the enemy of legal justification by a flawless universal ministry.

We humans have been defeated by breaking the law; Sin, death, the grave, and the devil, who have come to us without mercy through our transgression of the law (Rom. 5:12). These cannot be fought with material weapons, rather by closing the loopholes in the law; the penalty the law demands for the sinner is death (Rom. 6:23), for the Bible declares, "The soul that sinneth, it shall die" (Ezek. 18:4).

Therefore, it was known that freedom would come when the death penalty demanded by the law was fulfilled. So, the Torah law forgave sin through the atoning death, and continued to teach and instruct this until Christ. (Lev. 5:17-19) Thus it confirmed that "without shedding of blood there is no remission" (Heb. 9:22).

Since our Lord Himself carried the death on the cross on behalf of men that the law expected from men, the law lost its legal authority to hold men accountable; as a result, sin, death, the grave, and the devil were defeated, empty-handed and lost their legal authority to punish men. (1 Cor. 15:53-57) As a result, men entered directly into paradise free from sin, death, the grave, and the devil (Luke 23:43); in this process, life was obtained. It is from this perspective that we preach as the beginning of the cross is suffering, but the end is salvation;

From this perspective, the final result of the cross was forgiveness, mercy, peace, unity, freedom, victory over sin; death, the grave, and the devil. And since such power does not come from the creature but from God, it was interpreted as the preaching of the cross is the power of God to save.

Christ opened the grave and raises the dead, (Matt. 27:52) and said, "Today shalt thou be with me in paradise," (Luke 23:43) and He who casts out the devil saying "Hold thy peace, and come out of him" (Luke 4:35). This is the power of God; a human power cannot do this.

Therefore, until the day of the Lord comes, there is a temporary death and grave where we are separated from our earthly life and go to Him, but on the day of our Lord, death and the grave are permanently removed once and for all and the opportunity to live with our Lord in HIs kingdom with the power of endless life has been prepared for us, and our enemies have truly been defeated.

Today, we celebrate the Feast of the Cross, which we praise and worship God in a high-level worship service, to announce and proclaim this salvation to mankind. We preserve the preaching of the cross with honor and pass it on to future generations. Our reason for this is, the miraculous discovery of the true and original cross that was buried under mountain of rubbish.

The cross is a living witness and an eloquent preacher of the message of salvation, so it will be honored in our church forever. We will remember the preaching of salvation that the cross carried on its shoulders; we will remember it; and we will see our salvation through the crucifixion of our Lord with a refined spiritual eye.

May God bless our holiday.

May God bless Ethiopia and its people.

Glory be to God; Amen.

Abba Matthias I

Patriarch of Ethiopia Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. TekleHaimanot
September 26, 2024, Addis Ababa, Ethiopia

September 26, 2026 AD.
Addis Ababa, Ethiopia



Message of General Manager

"For He Himself is our peace, who has made both one."
He is our peace, who made Jews and Gentiles one.
(Ephesians 2:14)

Beloved children of the Holy Church, compliments on reaching the Feast of the Holy Cross (Meskel) in peace and healthiness; may God bless us all.

The Feast of the Finding of the True Cross (Demera and Meskel), which we celebrate annually on September 26 and 27 (Meskerem 16 and 17 in the Ethiopian calendar), is a time when we commemorate the Holy Cross, the instrument of the great divine favor through which humanity was reconciled with God and the covenant of love and peace was sealed by His blood.

As St. John Chrysostom teaches us in his homily on the Cross and Reconciliation: "The Cross is our peace through which we are reconciled with God; the Cross is the great platform of peace where human salvation was accomplished, where fall gave way to mercy, and where hatred was overcome by reigning love." St. Yared also declared that the Cross, by which the world damaged by sin was saved, is the glory and adornment of Christians, saying:

"Today the Cross has shined the world that had decayed; through the beauty of Mary, it brought joy, becoming the grandeur of Christians."

God, who took on flesh and a rational soul from Our Lady Saint Virgin Mary, became man, and Our Lord and Savior Jesus Christ broke down the wall of hatred through the blood He shed on the Cross. As St. Paul states in his letter to the Ephesians: "For He Himself is our peace, who has made both one, and has broken down the middle wall of separation" (Ephesians 2:14). The Cross is our symbol of unity, peace, and reconciliation. Through the Cross, enmity was abolished, true peace, which cannot be found from man, was established, those who were far off were brought near, and equality was proclaimed for all people regardless of rank.

Today, our lives are guided by the Light that shines for the whole world, Christ Himself, through what He accomplished for us on the Cross. The Meskel-Demera we celebrate each year on Meskerem 16 is an act of faith through which we witness to the true Light, Christ, and the power of the Cross.

Beloved children of our Church:

Today, as we commemorate and honor the Cross, we must rise above in a spirit of peace, casting out all hatred, division, and suspicion from within us. St. Gregory of Nazianzus, in his teaching on peace, states: "We can only be reconciled with God when we are reconciled with our brother." The Cross rises up those who have fallen and reconciles those who are separated; it never divides person from person. The four ends of the Cross of Christ are hands outstretched in love, gathering all the peoples of the world into unity. The Cross teaches love, not vengeance.

Just as Our Lord, who was crucified on the Cross, offered forgiveness to those who mistreated Him, saying, "Father, forgive them, for they do not know what they do" (Luke 23:34), we too, as followers of Christ today, must embrace forgiveness, tolerance, and brotherly love. Especially during this festival, we must visit and show love to the poor, orphans, the

sick, and those in prison among us. True holiday joy is found only when we share what we have and wipe away the tears of others.

Currently, our world and its people are in a season where they need peace, love, and unity more than ever. Christ, the King of Peace, gave us His peace through His Holy Spirit, His Cross, and His Church, saying in the Gospel: "Peace I leave with you, My peace I give to you" (John 14:27). However, for us who receive it, peace is not merely a spoken word, but a reality expressed in action. Therefore, the peace of Christ must be reflected in our daily activities. Focusing on our differences, opposing one another, and fostering mutual hatred will tear us down and scatter our people. Therefore, we issue our fatherly call for all our people to prioritize reconciliation over hatred and mutual harm. To the youth, who are the hope of the Church and the nation, we entrust you not to be overcome by emotion and worldly thoughts, but to be built up in the love of the Cross and stand for unity, peace, and development.

We have a historical and spiritual responsibility to preserve and pass on to the next generation the traditions, history, culture, and spiritual order of the Meskel celebration handed down to us in peace and love by our fathers. Ever since Queen Helena brought forth the Cross from where it was maliciously buried, and especially since a piece of the True Cross (Gimade Meskel) entered our country, Ethiopia, this feast has been celebrated colorfully across our nation. Our Church has preserved the liturgical order and national values of this holiday, delivering them intact for the benefit of today's generation. In turn, we are expected to guard this heritage and transmit it to the future generation. Reflecting on the adversity of our past life and the salvation we gained through Christ on the Cross, we ought to give thanks.

May the Feast of the Cross be a time when the air of peace blows and the seeds of love are sown. Let us make this Meskel a holiday of spiritual transformation of the heart. Let us break down the darkness of hatred with the light of love, and demolish the walls of division through reconciliation and peace.

May the God of Saints protect our country Ethiopia and its people in peace, love, and unity; may He shield our people from famine, pestilence, war, and internal division; and may He multiply the blessings and grace of this feast upon us all.

May He make the Feast of the Cross a festival of peace, love, and unity!

Abba Sawiros

General Manager of Patriarchate
Head Office and Archbishop of
South-West Shewa and Sheger City Dioceses.



Message of the General Secretary of the Holy Synod

"And having made peace through the blood of His cross, by Him to reconcile all things unto Himself; by Him, I say, whether they be things in earth, or things in heaven."

(Colossians 1:20)

The Cross is Our Power

The Cross of our Lord and Savior Jesus Christ is, in the Christian life, the mystery of salvation, the symbol of peace, love, and victory, and the foundation of spiritual life. The boundless love and peace of God revealed through the Cross is the price of blood paid for humanity.

When the Holy Apostle Paul explains the Holy Cross of our Lord and Savior Jesus Christ, he teaches us the profound mystery of the Cross at length, stating: "For the preaching of the cross is to them that perish foolishness; but unto us which are saved it is the power of God." (1 Corinthians 1:18)

Indeed, when our Lord and Savior Jesus Christ shed His blood and broke His body on the Cross to save humanity, He transformed the Cross-once an instrument of execution for criminals-into an emblem of peace and a weapon of victory over the enemy for us Christians. Thus, the sin that hung over humanity was defeated, death was humbled, the peace of mankind-which had been lost for ages-was established, man was reconciled with God, and eternal life was revealed.

The mystery of the Cross is not something we merely contemplate annually during the Feast of the Finding of the True Cross (Meskel) in September; rather, it is a reality we live daily in our Christian walk. Exalting the Cross means not merely wearing its symbol around our necks or embroidering it on our garments, but practically manifesting the teachings of the Cross in our lives. A life centered on the Cross means living a life of humility, sacrifice, love, and obedience.

When our Lord Jesus Christ taught us, "If any man will come after Me, let him deny himself, and take up his cross, and follow Me," He clarified that Christian life is unthinkable apart from the Cross. Therefore, to us, the Cross is not merely an ornament worn around the neck, but the mystery of salvation, the way of life, and the symbol of spiritual struggle. (Matthew 16:24)

The Holy Cross of our Lord Jesus Christ is the mystery of salvation; without the Cross, there is no salvation, and without salvation, there is no Christianity. This is why the Church continuously teaches that the Cross is the symbol (emblem) of our salvation and the source of our peace.

Although humanity endured suffering for many ages after transgressing God's commandment and being banished from Paradise, mankind was restored to its former glory and identity through Christ, who was crucified on the mount of Golgotha. The death brought by Adam was conquered through the Cross by the Second Adam, Christ. The mystery of the Cross is the great divine event wherein the love of God was practically demonstrated.

St. John teaches us that love is the foundational reason for the Cross, saying: "For God so loved the world, that He gave His only begotten Son, that whosoever believeth in Him should not perish, but have everlasting life." The Cross is the manifestation of love; God did not express His love in words alone, but demonstrated it by giving Himself on the Cross. (John 3:16)

The blood of Christ shed on the Cross is the work of salvation that liberated man from sin, death, and the bondage of Satan. That is why the Apostle Paul declared: "He made peace

through the blood of His cross," for the broken fellowship between man and God was reconciled through the Cross. (Colossians 1:20)

Even though the world exhibits many changing behaviors across different eras, the message of the Cross remains an unchangeable, eternal truth. Humanity, long fallen into sin, fear, loneliness, and spiritual weakness, has been granted hope, love, and salvation through the redemption of the Cross.

The generation of our time often loses its inner peace by chasing wealth, power, and worldly pleasures. However, the mystery of the Cross teaches us that true peace is found only in communion with Christ. Furthermore, the love revealed on the Cross leads man out of selfishness into love for God and neighbor.

The power of the Cross is manifested in a Christian's life through steadfastness of faith. The Cross teaches us not to despair in times of distress, to trust in God amidst trials, and to endure during temptations-because Christ showed us through His life that resurrection follows the Cross. To us, the Cross is the power of witness.

When we manifest the love of the Cross in our lives, we become living witnesses of Christ to the world. We must testify of the Cross not only through our words, but through our actions, humility, forgiveness, and love.

When the Church celebrates the Feast of the Cross, she does not merely recall past history; she calls us today for the work of the Cross to continue within our hearts. She teaches us to let the Cross be the principle of love and peace in our homes, families, social lives, and personal journeys.

In summary, the mystery of the Cross is revealed in a Christian's life through faith, love, humility, forgiveness, and spiritual struggle.

The Cross is not merely a history of yesterday, but the path of our life today. Christ revealed His love to us unto the end on the Cross; we too must receive that love and manifest it in our lives. Honoring the Cross means living with Christ; loving the Cross means choosing the path of love, salvation, and resurrection.

Likewise, based on the deep love shown by our Lord and Savior Jesus Christ through offering Himself on the Cross and the salvation He bestowed upon us, we Ethiopians are expected to live clothed in love and humility through mutual counsel, respect, and understanding, striving for the brightness of our nation's future.

